# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 192 መጋቢት 12 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









የኢንዱስትሪ ፓርኮች መስፋፋት የሀገር ውስጥ ምርት እንዲጨምር እድል ፈጥረዋል

# የሀገር ውስጥ ምርቶችን የመግዛት አስገዳጅነት ፋይዳ ምንድነው?

ዳግማዊት አበበ

ኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ በርካታ ምርቶች እያመረተች ትገኛለች። ሆኖም የመንግሥት ተቋማትም ሆኑ ማህበረሰቡ እነዚህን ምርቶች መጠቀም ላይ ያለው ፍላጎት እና አሠራር ክፍተት እንዳለበት ይነገራል።

ሰሞኑን ታዲያ ይህንን ክፍተት ለማሻሻል "የትኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ኢትዮጵያ ያመረተችውን ምርት ቀድሞ መግዛት አለበት። ምርቱን ካጣ ብቻ ወደ ውጭ እና ወደ ዓለም ገበያ መሄድ አለበት" የሚል ውሳኔ መተላለፉን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ገልጸዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለይ የሀገር ውስጥ ምርትን ማበረታታት ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚኖረው ፋይዳ ምንድነው? ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ ምን መሠራት አለበት? በሚሉ ሃሳቦች ላይ የምጣኔ ሀብት ምሁራን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።


የሀገር ውስጥ ምርቶችን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል












አቶ በርኦ ሀሰን

## በአዲስ አበባ 60 የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኃይል መሙያ ማሽኖች ተገጥመዋል

- በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከ100 ሺህ ተሻግሯል


ገጽ 6


# ታንዛኒያ የኤሌክትሪክ ኃይል ከኢትዮጵያ ለመግዛት መስማማቷ የሀገራቱን ግንኙነት ያጠናክራል

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- ታንዛኒያ የኤሌክትሪክ ኃይል ከኢትዮጵያ ለመግዛት መስማማቷ በሁለቱ ሀገራት መካከል ሁሉን አቀፍ ግንኙነት ለማጠናከር ይረዳል ሲሉ በታንዛኒያ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ሽብሩ ማሞ አስታወቁ፡፡

በታንዛኒያ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ሽብሩ ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ታንዛኒያ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ካላቸው የአፍሪካ ሀገራት መካከል አንዷ ናት፡፡ በተለይ እያደገ ከመጣው የሀገሪቷ ኢኮኖሚና የሕዝብ ቁጥር አንጻር የኃይል አቅርቦት ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች።

በአንጻሩ ኢትዮጵያ ለቀጣናው የኤሌክትሪክ ኃይል እያቀረበች መሆኑን የጠቀሱት አምባሳደሩ፤ ታንዛኒያ የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎቷን ለማሟላት ከኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ለመግዛት ስምምነት አድርጋለች፡፡ ይህም የኤሌክትሪክ ኃይል የንግድ ትስስር በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ሁሉን አቀፍ ግንኙነት ከማጠናከር ረገድ ጉልህ ሚና ይኖረዋል ብለዋል፡፡

እንደ አምባሳደር ሽብሩ ገለጻ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በታንዛኒያ በነበራቸው ጉብኝት በሁለቱ ሀገራት መካከል ቀደም ሲል ተፈርመው ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ ያልገቡ ስምምነቶች ወደ ተግባር እንዲገቡ መነቃቃትን የፈጠረ ነው፡፡

ጉብኝቱ በሁለቱ ሀገራት መካከል በግብርና፣ በኢነርጂና በአየር መንገድና በረራ ዙሪያ አዳዲስ ስምምነቶችን ለመፈራረምና መልካም ተሞክሮዎችን ለመጋራት ትልቅ እድል የፈጠረ መሆኑን ገልጸው፤ ይህም የሁለቱን ሀገራት የአቬሽንና ኢነርጂ ዲፕሎማሲን የሚያጠናክር ነው ብለዋል፡፡

በታንዛኒያ የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽነት ከ36


ታንዛኒያ የኤሌክትሪክ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




አምባሳደር ሽብሩ ማሞ









አቶ ግዳልቅ አልቅሚ

# ክልሉ ለበልግ ወቅት የግብርና ሥራዎች ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ለአርሶ አደሩ እያቀረበ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ለበልግ ወቅት የግብርና ስራዎች የአፈር ማዳበሪያና የምርጥ ዘር ግብዓት ለአርሶ አደሩ ተደራሽ የማድረግ ስራ እየተሰራ ነው ሲል የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ግብርና ቢሮ የግብርና ግብዓት ዘርፍ ምክትል ኃላፊ የሆኑት አቶ ግዳልቅ አልቅሚ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በበልግ ወቅት አብዛኛው የእርሻ መሬት በዘር የመሸፈን ስራ ይከናወናል፤ በበልግ የሚዘሩ አዝርቶች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲዘሩ በአሁኑ ጊዜ የአፈር ማዳበሪያና የምርጥ ዘር ግብዓት ለአርሶ አደሩ ተደራሽ እየተደረገ ነው።

በክልሉ የግብርና ግብዓት እጥረት እንዳይከሰት ከጥቅምት ወር ጀምሮ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ገልጸው፤ በበልግ ወቅት የሚዘሩ የእርሻ መሬቶችን በዘር ለመሸፈን የአፈር ማዳበሪያና የምርጥ ዘር ግብዓት ተደራሽ የማድረግ ስራ እየተከናወነ ነው ብለዋል።

የግብርና ስራዎችን ለማሳለጥ ለአርሶ አደሩ የአፈር ማዳበሪያና የምርጥ ዘር ግብዓት ወቅቱን ጠብቆ ማቅረብና ተደራሽ ማድረግ ተገቢ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በ2014/15 የምርት ዘመን በተከሰተ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት እጥረት ሳቢያ ክልሉ ማምረት የሚገበውን ምርት ማምረት አልቻለም ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ባለፈው ዓመት የተከሰተው የአፈር ማዳበሪያ የአቅርቦት ችግር በዘንድሮው የምርት ዘመን እንዳይደገም የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ ብለዋል።

በ2016/17 የምርት ዘመን የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ችግር እንዳይከሰት 830 ሺህ ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ወደ ክልሉ እንዲገባ ታቅዶ እየተሰራ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ በአንደኛ ዙር ከተገዛው የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ 189 ሺህ 301 ኩንታሉ ወደ ክልሉ ገብቶ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ተደርጓል፤ ቀሪውን ከወደብ እንዲጓጓዝ የማድረግ ስራ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

የአፈር ማደባሪያ ዋጋ እንደ አካባቢው ርቀት እንደሚለያይ ጠቀሰው፤ከሶስት ሺህ 890 እስከ አራት ሺህ 200 ብር ዋጋ ለአርሶ አደሩ እየቀረበ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በክልሉ የምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ምርጥ ዘር ለአርሶ አደሩ ተደራሽ የማድረግ ስራ እየተሰራ ነው ያሉት የአቶ ግዳልቅ፤ ለ2016/17 የምርት ዘመን 43 ሺህ ኩንታል ምርጥ ዘር ለበልግ እርሻ ተደራሽ ለማድረግ የታቅዶ ሲሆን፤ እስካሁንም 22 ሺህ 90 ኩንታል የበቆሎ፣ የማሽላና የስንዴ ምርጥ ዘር ለአርሶ አደሩ ተደራሽ የማድረግ ስራ ተከናውኗል ብለዋል።

በተያዘው የምርት ዘመን የአርሶ አደሩ የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት በተለየ ሁኔታ ጨምሯል፤ የአርሶ አደሩን የአፈር የማዳበሪያ ፍላጎት ለማሟላት የአፈር የማዳበሪያ በፍጥነት የማቅረብ ስራ እየተሰራ ነው ሲሉ አመልክተዋል።

# ከተሞች የግንባታ አስተዳደር ችግራቸውን ለመቅረፍ የቴክኖሎጂ አቅማቸውን ማሳደግ አለባቸው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ከተሞች ያለባቸውን የግንባታ አስተዳደር ችግር ለመቅረፍ የቴክኖሎጂ አቅማቸውን ማሳደግ እንዳለባቸው የኢትዮጵያ ከተሞች ትብብር መድረክ አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ከተሞች ትብብር መድረክ ዋና ዳይሬክተር አቶ አንዷለም ጤናው ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በከተሞች ላይ የሚሰጡ አገልግሎቶች ዘመናዊነትን የተከተሉ አይደሉም፡፡ ዘመናዊ የግንባታ አስተዳደርን ከመጠቀም አንጻር ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ ከዚህ መነሻነት ከተሞች የግንባታ አስተዳደር ችግራቸውን ለመቅረፍ የቴክኖሎጂ አቅማቸውን ማሳደግ አለባቸው፡፡

የከተሞችን የግንባታ አስተዳደር ችግር ለመቅረፍ በተለይ በፕሮጀክቶች አስተዳደር ቴክኖሎጂ፣ በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎትና በመሠረተ ልማት ቅንጅታዊ አሰራር ላይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም የስማርት ሲቲ ግንባታዎችን ማፋጠን አለባቸው ሲሉ አስረድተዋል።

ከተሞች ያላቸውን የተማረ የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ በመጠቀም አገልግሎት አሰጣጣቸውን ማዘመን፤ በተለይ በማዘጋጃ ቤቶች አገልግሎት ላይ ትኩረት ማድረግ፤ የመልካም አስተዳደር ችግር መፍታትና ከከተማ ግንባታዎች አንጻር የተቀመጡ ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓቶችን መጠቀም እንዳለባቸውም ጠቁመዋል፡፡

የከተሞች ፎረም መዘጋጀት ከተሞች አንዱ ካንዱ የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ፣ ተመሳይይ ችግር ያለባቸው ከተሞች ለጋራ ችግራቸው የጋራ መፍትሄ እንዲፈልጉ እንደሚያስችልም ተናግረዋል፡፡

ትብብርን በማጠናከር በኩልም በፎረሙ ላይ አራት ከተሞች በጋራ ለመስራት ስምምነት ማድረጋቸውን በመጠቀስ፤ በዝግጅቱ ላይ አራት ከተሞች በጋራ ለመስራት ስምምነት መፈራማቸውን ጠቁመዋል፡፡

በቀጣይ የከተሞች ፎረም በአፋር ብሔራዊ ክልል በሰመራ ሎጊያ እንደሚከበር የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለቀጣይ የሚታዩ ነገሮችን ኤሌክትሮኒክስ በሆነ መልኩ ለማሳየት እና ጥናቶችን በማቅረብ ሰፊ ውይይት ለማድረግ እቅድ መያዙን አስረድተዋል፡፡

መድረኩን የሚያዘጋጁት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ከተሞች ትብብር መድረክ በጋራ በመሆን ነው፡፡ ላለፉት አራት ዓመታት በኮሮና ወረርሽኝ እና በአንዳንድ ሀገራዊ ምክንያቶች ሳይከበር መቆየቱ ተገልጿል ፡፡በቅርቡ የከተሞች ፎረም በወላይታ ሶዶ ከተማ በድምቀት መካሄዱ ይታወሳል፡፡



አቶ አንዷለም ጤናው



# ኢትዮ ቴሌኮም ለ500 አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ድጋፍ አደረገ

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ለሚገኙ 500 አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የስምንት ሚሊዮን ብር ቁሳቁሶች ድጋፍ አደረገ።

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ቁሳቁሶቹን ትናንት ተረክበዋል፡፡ በወቅቱ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ አካልጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን ዋና ዳይሬክተር አቶ አባይነህ ጉጆ እንደተናገሩት፤ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የተደረገው የቁሳቁስ ድጋፍ ስምንት ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎበታል፡፡

የተደረገው የቁሳቁስ ድጋፍ ተሽከርካሪ ወንበር፣ ክራንች ፣ የዓይነስውራን በትር እና መስማት ለተሳናቸው የሚሆን የጆሮ ማዳመጫ መሆኑን ገልጸው፤ ድጋፉ በሀገሪቱ ለሚገኙ 500 አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት፤ የአካል ጉዳተኞች ማህበር በሀገሪቱ የሚገኙ አካል ጉዳተኞችን ለመርዳት በርካታ ስራዎች እየሰራ ይገኛል፡፡ የተደረገው ድጋፍ አካል ጉዳተኞችን ለመርዳት የሚደረገውን ስራ የሚያጠናክር መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የድጋፍ ቁሳቁሶችን እንዲያደርግ ከፌደሬሽኑ የቀረበለትን ጥያቄ ተቀብሎ ላደረገላቸው ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ 199 አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የድጋፍ ቁሳቁሶችን ትናንት መረከባቸውን ገልጸው፤ ድጋፉም 62 ተሽከርካሪ ወንበር፣ 25 ክራንች፣ 59 የአይነ ስውራን በትር እና 53 የጆሮ አጋዥ ማዳመጫ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡



አቶ አባይነህ ጉጆ

በቀጣይ በሌሎች ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ድጋፉ እንደሚሰራጭ አመላክተዋል፡፡

የኢትዮ ቴሌኮም ቺፍ ኮሙኒኬሽን ኦፊሰር አቶ መሳይ ውብሸት በበኩላቸው፤ ኢትዮ ቴሌኮም ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት በርካታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

ተቋሙ የዜጎች ሁለንተናዊ ዕድገት ለማረጋገጥ በጤና፣ በሰብዓዊ ድጋፎች፣ በትምህርትና በአረንጓዴ ልማት አካታችና ዘላቂ መፍትሄ የሚሆኑ ተግባራቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል።



አቶ መሳይ ውብሸት

አንዳንድ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ድንቅ ብቃት አላቸው ያሉት አቶ መሳይ ፤ እነዚህን ተማሪዎች ማገዝ የነገዋን ብሩህ ኢትዮጵያ ለመገንባት ለሚደረገው ጥረት አካል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በመጨረሻም አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ጠንክረው በመማር ለራሳቸውና ለሀገራቸው የሚጠቅሙ ስራዎችን ለማከናወን ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

ዜና

# በኢትዮጵያ 8 ሺህ ከተሞችና የገጠር መንደሮች
## የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በኢትዮጵያ ስምንት ሺህ ከተሞችና የገጠር መንደሮች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የአገልግሎቱ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አገልግሎቱ ለነባር ደንበኞች አስተማማኝ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለማቅረብና ለአዳዲስ ደንበኞችም ፍትሐዊ የኃይል አቅርቦት ለመፍጠር በትኩረት እየሠራ ይገኛል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ስምንት ሺህ ከተሞችና የገጠር መንደሮችን የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

አገልግሎቱ የኤሌክትሪክ ኃይልን ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በጅምላ በመግዛት ለደንበኞች ተደራሽ የማድረግ ሥራ እንደሚሠራ ጠቁመው፤ አስፈላጊውን የቆጣሪ ገጠማና የቴክኒክ ስራዎች በማከናወን ህብረተሰቡን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን እየተደረገ መሆኑን አስረድተዋል።



**አቶ መላኩ ታዬ**

አዳዲስ ደንበኞችን ተደራሽ ለማድረግ የተዘረጉ መሠረተ ልማቶችን በመጠቀምና ከመሠረተ ልማት ውጭ ያሉትን ደግሞ በዋናነት የፀሐይ ኃይልና ሌሎች አማራጮች በመጠቀም ደንበኞቹን እያስተናገደ መሆኑን አመልክተዋል።

በየካቲት ወር ብቻ በተለያዩ አማራጮች 33 ሺህ 711 አዳዲስ ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ያሉት አቶ መላኩ፤ ይህን ተከትሎ በቤተሰብ ደረጃ ቆጣሪ ገብቶላቸው አገልግሎት እያገኙ ያሉ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ደንበኞች አራት ሚሊዮን 615 ሺህ 787 መድረሳቸውን አስታውቀዋል።

ቆጣሪ ከገባላቸው ውስጥ ሦስት ሚሊዮን 730 ሺህ 356 ደንበኞች የድህረ ክፍያ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ሲሆኑ፣ የቅድመ ክፍያ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ደግሞ 885 ሺ 431 መሆናቸውን ገልጸዋል።

እንደሀገር የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽነት ላይ ውስንነት መኖሩን ጠቅሰው፤ ችግሩን ለመቅረፍም በገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም አማካኝነት ሽፋኑን ለማሳደግ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በተሠራው ሥራም በ1998 ዓ.ም ፕሮግራሙ ሲጀመር በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ600 ያልበለጠው የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ የሆኑ የከተሞች ቁጥር፤ አሁን ላይ 8 ሺህ ከተሞችና የገጠር መንደሮች ላይ መስፋፋቱን አስረድተዋል፡፡

ባለፈው የካቲት ወር ብቻ 11 ከተሞችና የገጠር መንደሮች የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ሆነዋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በዚህም ለሁለት ሺህ 768 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር አስችሏል ሲሉ ተናግረዋል።

የኤሌክትሪክ ኃይልን ለእያንዳንዱ ዜጋ ለማዳረስ የሚደረገው ጥረት የማህበረሰቡ የተበታታነ አሰፋፈርና መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ በእጅጉ እየፈተነው መሆኑን አመላክተው፤ ችግሩን ለመቅረፍም ከዋናው የኤሌክትሪክ ቋት ባለፈ ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ለማድረስ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

አዳዲስ ደንበኞችን የኃይል ተጠቃሚ ከማድረግ ጎን ለጎን ለነባር ደንበኞች አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት እንዲኖር በትኩረት እየተሠራ መሆኑን አስታውሰው፤ ዛሬ ያለውን ብቻ ሳይሆን ነገ የሚመጣውንም ደንበኛ ታሳቢ ያደረገ የመሠረተ ልማት ማሻሻልና መልሶ ግንባታ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው ብለዋል።

አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎችም ክልል ከተሞች እየተሠራ ያለው የመሠረተ ልማት ማሻሻያና መልሶ ግንባታ ሥራ የኤሌክትሪክ አቅርቦት መቆራረጡን ችግር ቢቀንሰውም ሙሉ በሙሉ ማስቀረት እንዳልተቻለ ጠቅሰው፤ አገልግሎቱ የማህበረሰቡን ፍላጎት የሚያሟላ ኃይል ለማቅረብ ትኩረት ሰጥቶ ሰፊ ሥራ እያከናወነ መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡



# ዩኒቨርሲቲው 71 የእንሰት ዝርያዎች
## ከመጥፋት መታደግ ችሏል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ እየሰራቸው ባሉ የማህበረሰብ አቀፍ የምርምር ሥራዎች 71 የእንሰት ዝርያዎች ከመጥፋት መታደግ መቻሉን አስታወቀ፡፡

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የምርምር፣ የማኅበረሰብ አገልግሎትና የቴክኖሎጂ ትራንስፈር ምክትል ፕሬዚዳንት ዮሐንስ ገብሩ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ዩኒቨርሲቲው እየሰራቸው ባሉ የማህበረሰብ አቀፍ የምርምር ሥራዎች 71 የእንሰት ዝርያዎች ከመጥፋት መታደግ ችሏል፡፡

በአፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲዎች ከተካተቱ 15 ዩኒቨርሲቲዎች መካከል አንዱ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ነው ያሉት ዶክተር ዮሐንስ፤ ዩኒቨርሲቲው የምርምር የማኅበረሰብ አገልግሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎችን እየሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው የፈርዝዬ የእንሰት ምርምር ማዕከል አቋቁሞ በእንሰት ዙሪያ እየሰራ መሆኑን ዶክተር ዮሐንስ ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም ምቄ የሚባል የቡና እና የፍራፍሬ ምርምር የሚካሔድበት ጣቢያ እንዳለው አስረድተዋል፡፡

ሁሉም ዝርያዎች የየራሳቸው ጠቀሜታ እንዳላቸው የጠቆሙት ኃላፊው፤ ዝርያዎች እንዳይጠፉ ማድረግ፣ በሽታን የመከላከል ሒደት ማሻሻል፣ የአሰራር ሂደትን ማዘመን እንዲሁም የተለያዩ ማሽነሪዎችን ማፍለቅ በምርምር ማዕከሉ ከሚሰሩ ሥራዎች መካከል ተጠቃሽ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

እንደ ዶክተር ዮሐንስ ገለጻ፤ በተሰሩ የምርምር ሥራዎች የእናቶችን ድካምና ጊዜ መቀነስ እንዲሁም በእንሰት ላይ የሚከሰቱ የተለያዩ በሽታዎችን መከላከል ተችሏል፡፡ በተለይ በማሽነሪ ለማምረት በተደረገ ጥረት ሁለት ማሽኖች በመስራት በቅርቡ ሰርቶ ማሳያ ላይ ሙከራ መደረጉን አመልክተዋል፡፡

ማሽኖች ተሻሽለውና ያሉባቸው ችግሮች ተፈትተው ለእያንዳንዱ አርሶ አደር ለማዳረስ ባይቻል እንኳን በጋራ የተደራጁ ወጣቶችን በማዋቀር የእንሰት ወፍጮ ቤት በወረዳው ላይ ለማቋቋም እቅድ እንደተያዘም ነው ዶክተር ዮሐንስ የገለጹት፡፡

አንዳንዶቹ የእንሰት ዝርያዎች ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉ ናቸው ያሉት ዶክተር ዮሐንስ፤ የእንሰት ተረፈ ምርት ከአሸዋና ከጠጠር ጋር ተደባልቆ ለአስፋልት ጥንካሬ ይሰጣል የሚል እሳቤ በመኖሩ በሲቪል ኢንጂነሪንግ ጥናት እንዲሰራ የሚደረግ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

እንሰት የምግብ ዋስትናን እና የአየር ንብረት ተፅዕኖ ላይ ያለው ሚና ለማረጋገጥ በአግሪካልቸራል ኢኮኖሚክስ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች አሉ ያሉት ዶክተር ዮሐንስ፤ እንሰት ከምግብነት በተጨማሪም ከተረፈ ምርቱ ለመኝታ አገልግሎት እንዲሁም ጥራት ያለው ወረቀት ለማምረት እንደሚያስችል አስታውሰዋል፡፡

# ዩኒቨርሲቲው የምግብ ዋስትናን
## ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥራዎች ላይ በትኩረት እየሠራ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

<u>ቦንጋ</u>፡- ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ እንደሀገር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተያዘውን እቅድ ለማሳካት ከአካባቢው የመልማት ጸጋ ጋር በማቀናጀት እየሠራ መሆኑን አስታወቀ። ዩኒቨርሲቲው በአምስት የቡና ጣቢያዎች ሁለት ሚሊዮን የተለያዩ የቡና ዝርያዎችን እያለማ ነው።

የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክስ ምርምር ቴክኖሎጂ ሽግግርና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ከለላው አዲሱ(ዶ/ር) ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው ከተመሰረተ ስድስት አመቱ ቢሆንም ባጭር ጊዜ ውስጥ ከአካባቢው ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ያለውን የመልማት ጸጋ ማህበረሰቡ በአግባቡ እንዲጠቀም ለማስቻል የተለያዩ የምርምር ስራዎችን እየሰራ ነው።

እንደ ዶክተር ከለላው ገለጻ፣ ክልሉ በቡና፣ በማር፣ በኮረሪማ፣ በእንሰት፣ በበግ እርባታና ሌሎች ዘርፎች ላይ ያለውን አቅም በጥናት የተመሰረተ ስራ በማከናወን የማህበረሰቡን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ሰፊ ስራ እያከናወነ ነው። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የቦንጋ በግ፣ የበሬ ማድለብ፣ የወተት ላም፣ የቡና ልማት፣ የሙዝ፣ የአናናስና የአፕል ፍራፍሬዎችን ምርት ለማባዛት ተግባራዊ ምርምሮችን እያካሄደ ነው።

ዩኒቨርሲቲው ለምርምር የሚሆኑ ቦታዎች በክልሉ ባሉ ዞኖችና ወረዳዎች የምርምር ቦታዎችን ተረክቦ ለአርሶ አደሩ ችግኞች ለማሰራጨት እየሰራ መሆኑን የገለጹት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ በተለይም ሀገራዊ አቅጣጫ ከሆነው የሌማት ትሩፋት ጋር ቁርጠኝነት ያላቸው እንደ ዶሮ እርባታ፣ የወተት ላሞች እርባታና ማዳቀል ስራ በመስራት ውጤታማ ስራ መስራቱን ገልጸዋል።

ዶክተር ከለላው እንደሚሉት፤ በሚያከናውነው የሌማት ስራ ስራአጥ ሴቶችን በማደራጀት ወተት፣ እንቁላል፣ ሙዝና ሌሎች አትክልትና ፍራፍሬዎችን የሚሸጡበት ሱቅ አመቻችቷል። በተጨማሪም በማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ጧሪ ለሌላቸው 54 አረጋውያን



ፎቶ ሀዱሽ አብርሀ

**ከለላው አዲሱ(ዶ/ር)**

የማይቋረጥ ድጋፍ እያደረገ ሲሆን በዘላቂነት የሚኖሩበት ጤና ጣቢያ ያለው የመኖሪያ ቤት ግንባታም አካሂዷል።

ዩኒቨርሲቲው ለመጀመሪያ ጊዜ በመጀመሪያ ዲግሪ 37 እንዲሁም በሁለተኛ ዲግሪ 12 ተማሪዎችን በቡና ቴክኖሎጂ እንደሚያስመርቅ የተናገሩበት ዶክተር ከለላው፣ በአምስት ጣቢያዎቹ 74 አንድ 10፣ 74 አንድ 12 እና 74 ፤ 54 የተባሉ የደጋ፣ የቆላና የመካከለኛ ቦታዎች ተስማሚ የሆኑ ሁለት ሚሊዮን የቡና ችግኞች መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጾሙ ለቀደመ ሀገራዊ እሴታችን ትንሳኤ እንዲሆን!

ኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖቶች መገኛ ሀገር ናት። ከሕዝቦቿም ከ90 ከመቶ በላይ የሚሆነው ሃይማኖተኛ እንደሆነ ይታመናል። ከዚህ የተነሳም እንደ ሀገር የብዙ ሃይማኖታዊ እሴቶች መገኛ ብቻ ሳይሆን፤ በነዚህ እሴቶች የተገሩ ብዙ ትውልዶችን ማስተናገድ የቻለች የረጅም ዘመን ዕድሜ ባለፀጋም ናት።

የሃይማኖቶቹ እሴቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ከፈጠሩት ፈሪሀ እግዚአብሔር / ፈጣሪን የመፍራት እሴት አንጻርም በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶች ፣ በፍቅር እና በመተሳሰብ ከፍያለ ማኅበራዊ መስተጋብሮችን ፈጥረው አብረው መኖር የቻሉበትን የታሪክ ገጾች ጽፈው ማለፍ ችለዋል። ይህም ለዘመናት ሀገራዊ መለያችን ሆኖ አገልግሎናል።

ፍቅር ከዚህ የሚመነጭ ወንድማማችነት ፣ ትህትና ከዚህ የሚመነጭ ወንድምን እስከ ጉድለቱ መቀበል ፣ ይቅር ባይነት ከዚህ የሚመነጭ ሆደ ሰፊነት ፣ ልግስና ከዚህ የሚመነጭ በክፉ ቀናት የሚገለጥ ቅንነት ...ወዘተ የቀደሙት ትውልዶች /አባቶቻችን የጋራ ስብዕናዎች ዋነኛ መገለጫ ነበሩ።

ልዩነቶችን በመቻቻል ፣ ከዛም ባለፈ ውበት አድርጎ ከማየት የተቀዱት ፣በዚህም ዘመናት ያስቆጠሩት ማኅበራዊ እሴቶቻችን ፣ እንደ ሀገር ለመጣንባቸው ረጅም ዘመናት ሆነ፣ በጠንካራ መሠረት ላይ ለተዋቀረው የሀገረ መንግሥት መንግሥት ታሪካችን አልፋና ኦሜጋ እንደነበሩም ይታመናል።

ይህም ከራሱ ይልቅ ለጎረቤቱ የሚያስብና ፣ መንገደኛ በፍቅር ተቀብሎ፣ አብልቶ፣ አጠጥቶ ፣ እግር አጥቦ መኝታውን ለቆ መሬት የሚተኛ ከፍ ያለ የሞራል ልእልና የተላበሰ ትውልድ በዘመናት መካከል መፍጠር አስችሏል። የማይቻሉ የሚመስሉ መንፈሳዊ /ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎችን መሬት አውርዶ በሕይወቱ መግለጽ የቻለ ትውልድ ተፈጥሮ በተጨባጭ ታይቷል።

ለቀጣይ ትውልዶች የሕይወት ስንቅ የሚሆኑ የሕይወት ልምምዶች ፤ለተሻለ አስተሳሰብ መሠረት ሊሆኑ የሚችሉ መንፈሳዊ እና ማኅበራዊ እሴቶች ፣ በነዚህ እሴቶች የተገሩ ማኅበራዊ ማንነቶች ተፈጥረው ፣ በነዚህም እንደ ሕዝብ ከፍ ያለ የሞራል ልዕልና ተላብሰናል። የታላላቅ ታሪክ ባለቤቶች መሆን የቻልንበትን አቅም ገንብተውልናል።

ክፉ በሚባሉ ቀናቶች ሳይቀር፤ በነዚህ ከፍ ባሉ የሞራል እሴቶች ተደግፈን ማኅበራዊ ማንነታችንን ሳናዛንፍ ዘመናትን መጓዝ ችለናል። በዚህም ለዓለም እንቆቅልሽ የሆንባቸው ክስተቶች በየዘመኑ ተፈጥረዋል። በእነዚህ የዘመኑን ተግዳሮቶች ተሻግረን ዛሬ ላይ መድረስ ፤ነገዎቻችንንም ተስፋ ማድረግ ችለናል።

የዛሬ ፈተናዎቻችን ምንጭ ይህንኑ እውነታ ተረድተን ማስቀጠል አለመቻላችን እንደሆነ የብዙዎች እምነት ነው። ከነዚህ ዘመን ተሻጋሪና አሻጋሪ እሴቶቻችን ጋር ያደረግነው ያልተጋባ ፍች እንደሆነም እንዲሁ ብዙዎች ይስማማሉ። የነገ ተስፋችን ተግዳሮትም ይሄው እውነት እንደሚሆን ለብዙዎች ጥያቄ አይደለም።

ከዚህ የተነሳ አሁን ላይ ይህንን እውነታ ቆም ብለን በሰከነ መንፈስና በጠራ አዕምሮ ልናጤነው፣ ደግመን ደጋግመን ልናስበው ፣ በተለይም ያለንበት ወቅት የታላላቅ ጾሞች ወቅት ከመሆኑ አንጻር አጋጣሚውን በአግባቡ ልንጠቀምበት ፣ ውስጣችንን በአግባቡ ተመልክተን ከራሳችን ጋር እርቅ ልንፈጥርበት ይገባል።

ካልተገባ ጥላቻ እና ጠብ ወጥተን ፤ከጠባችን እና ከተዘራብን ጥላቻ በስተጀርባ ያሉ ትርክቶችን በቀደሙት መንፈሳዊና ማኅበራዊ እሴቶቻችን መርምረን የጥላቻ እና የጥፋት ባርነት ራሳችን እና ማኅበረሰባዊ ማንነታችንን ነጻ ማውጣት ይጠበቅብናል።

ያለንበት የጾም ጸሎት ወር የትናንት ወንድማማችነታችንን ፣ ”አንተ ትብስ እኔ ... ” ለሚለውን የቀደመ የማንነት ሥሪታችን ትንሳኤ፣ ከተጣባን ራስ ወዳድነት እና ደንታ ቢስነት ወጥተን ከፍ ባለ የሞራል እሴት እንደ ሀገር በኃላፊነት መንፈስ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን የምንመራበትን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ መፍጠር የሚያስችል ሊሆን ይገባል። ለዚህ የሚሆን መንፈሳዊ ዝግጁነትም ከሁሉም የሚጠበቅ ይሆናል።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከቃላት ትርጓሜ በስተጀርባ የሚፈጠሩ ጥፋቶች

ሙሉቀን ታደገ

**በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማዕከል አተያይ ብሔር ማለት ምንድን ነው ? የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማዕከል በ1993 ዓ.ም በሳተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላት የመጀመሪያ እትም እንደ አመላከተው ብሔር ማለት —ሀገር ማለት ነው“ ሲል ትርጓሜ ሰጥቶታል**

በዓለም ታሪክ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የሚለው የፖለቲካ ጽንሰ ሃሳብ የተጀመረው ከኢንዱስትሪ አብዮት መጀመር ጋር ተያይዞ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ከዚያ በፊት ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የሚባል ቋንቋ በየትኛውም ዓለም ማንም አያውቀውም፤ አይጠቀመውም ነበር።

ኢትዮጵያም ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የሚለውን የፖለቲካ ጽንሰ ሃሳብ ሙሉ በሙሉ የተዋሰችው በኢንዱስትሪ አብዮት ታሽተው ካለፉ ሀገራት ፖለቲከኞች በተለይም ከሶሻሊስቶቹ ከነማርክስ ፣ሔንግልስ ፣ጆሴፍ ስታሊን እና ሌኒን የፖለቲካ ፍልስፍና ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን ቃላቶች የምንተረጉምበት እና የምንጠቀምበት አግባብ ግን ጽንሰ ሃሳቡ ያዋሱ ሶሻሊስቶች እና ኢፔሪያሊስቶች ከሚሰጡት ትርጓሜ የተለየ እና ፈጽሞ ዝምድና የሌለው ነው።

ለመሆኑ ሶሻሊስቶች እና ኢፔሪያሊስቶች እንዲሁም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማዕከል ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የሚሉት ቃላት እንዴት ይተረጎማሉ? በተለይ ብሔር ማለት ምን ማለት ነው? ፖለቲከኞቻችን ሳይገባቸው እና ሳይቸግራቸው የተዋሷቸውን ቃላቶች እንዴት እየተጠቀመባቸው ነው? ምን የሚልስ ትርጓሜ ሰጧቸው? የሚለውን በወፍ በረር ላስመልክታችሁ። ከዚህ በመነሳትም “በኢትዮጵያ የትኛው ጎሳ ነው ብሔር መሆን ይቻላል?” የሚለውን መልስ ማግኘት ትችላላችሁ።

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማዕከል አተያይ ብሔር ማለት ምንድን ነው ? የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማዕከል በ1993 ዓ.ም በሳተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላት የመጀመሪያ እትም እንደ አመላከተው ብሔር ማለት “ሀገር ማለት ነው” ሲል ትርጓሜ ሰጥቶታል። ይህ መዝገበ ቃላት በሁለተኛ ደረጃ በሰጠው ትርጉም “ብሔር ማለት አንድ አይነት ቋንቋ ያለው ፤ አንድ አይነት ባህል እና ስነ ልቦናዊ አመለካካት ያለው፣ በታሪክ፣ በኢኮኖሚ የተሳሰረ እና በተወሰነ ክልል ውስጥ የሚኖር ህዝብ ነው” ሲል ያስረዳል።

በሶሻሊስቶች እና በኢፔሪያሊስቶች አተያይ ብሔር ማለት ምንድን ነው ?

በሶሻሊስቶች እና በኢፔሪያሊስቶች አንድ ማህበረ ሰብእ ብሄር ለመባል የግድ ስድስት ነገሮችን ማሟላት እንዳለበት ይጠቁማሉ። ከእነዚህ መካካል አንደኛው ለረጅም ዘመናት በታሪክ የተቀናጁ ማህበረ ሰብእ መሆን አለባቸው የሚል ነው። ከዚህ አንጻር “ብሔር ማለት በዘር ወይም በጎሳ ላይ የተመሰረተ ማህበር ማለት አይደለም” ሲሉ ያስረዳሉ።

ለምሳሌ የጣሊያን ብሔር የተመሰረተው ከሮማዊን፣ ከቲውቶን ፣ከኢትሩስካን ፣ከግሪክ ፣ከአረብ እና ከመሳሰሉት ጎሳዎች ነው ። ግን ጣሊያን አንድ ብሄር ናት። እነዚህ ጎሳዎች ተጠራቅመው የጣሊያን ብሔር የተባሉት የተለያዩ ጎሳዎች በፈጠሩት ስብጥር ሳይሆን ጎሳዎቹ ለበርካታ ዘመናት በታሪክ የተቆራኙ ማህበረ ሰብእ ስለሆኑ ነው። በተመሳሳይ አንድ ጎሳ ብቻ ያለው ማኅበረሰብ ለበርካታ ዘመናት በታሪክ ያልተቀናጀ ከሆነ ብሔር ሊባል አይችልም።

ሌላኛውና ሁለተኛው አንድን ማህበረ ሰብእ ብሔር ሊያስብል የሚችለው ለበርካታ ዘመናት በታሪክ ስለተቀናጀ ብቻ አይደለም። ይልቁንም በታሪክ የተቀናጁት ማህበረሰቦች “የጸና ማህበረ ሰብ” መሆን ሲችሉ ነው።

ሦስተኛው የኢፔሪያሊስቶች መስፈርት ደግሞ ቋንቋ ነው። አንድ ማህበረሰብ ለዘመናት በታሪክ የተሳሰረ እና የጸና ማህበረሰብም ቢሆን አንድ አይነት ቋንቋ መናገር ካልቻሉ ብሔር ሊባል እንደማይችል ያስረዳሉ።

ይሁን እንጂ ይህ ማለት የተለያዩ ብሔሮች ሁልጊዜ እና የትም የተለያዩ ቋንቋዎች ይናገራሉ። አሊያም አንድ አይነት ቋንቋ የሚናገሩ ሕዝቦች ሁሉ አንድ ብሔር ናቸው ማለት አይደለም። በአንድ ጊዜ በተመሳሳይ ሰዓት በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ ማህበረሰቦች ተመሳሳይ ቋንቋዎችን ቢጠቀሙም አንድ ብሔር ናቸው ማለት አይደለም።

ለምሳሌ እንግሊዞች እና አሜሪካኖች ሁለቱም የሚናገሩት እንግሊዝኛ ነው። ነገር ግን የተለያዩ ሀገራት ናቸው። በተመሳሳይ ኖርዌጅያኖችና ዴኒሾች ተመሳሳይ ቋንቋ ይናገራሉ። እንዲሁም እንግሊዞች እና አይሪሾች አንድ አይነት ቋንቋ ያወራሉ። ነገር ግን አንድ ብሔር አይደሉም።

ስለዚህ አንድ ማህበረሰብ ብሔር ለመባል አንድ አይነት ቋንቋ ከማናገር ፣ አንድ አይነት ታሪክ ከመኖር እና የጸና ማህበረሰብ ከመሆን ባለፈ በአንድ በተወሰነ የሀገር ወሰን ውስጥ መኖር የግድ ይለዋል። እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን አንድን ማህበሰብ ብሔር ከሚያስብሉት የኢፔሪሊስቶች እና የሶሻሊስቶች መስፈርቶች መካከል “በአንድ በተወሰነ የሀገር ክልል ውስጥ መኖር” የሚለው አንዱ መሆኑ ነው።

ነገር ግን አንድ ማህበረሰብ አንድ አይነት ቋንቋ ፣ ታሪክ ፣ የፀና ማህበረሰብ እና በአንድ ሀገር ስለኖረ ብቻ ብሔር መባል አይችልም። ስለሆነም ብሄር ለመባል በኢኮኖሚ ሥርዓት መተሳሰር የግድ ይለዋል።

በአንድ ማህበረሰብ ብሔር ለመባል የመጨረሻው መስፈርት ደግሞ ማህበረሰቡ አንድ አይነት ስነልቦናዊ ዘይቤ ሲኖረው ነው። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ቃላቶችን የተዋስናቸው ማርክሲስቶች እና ኢምፔሪያሊስቶች አጥብቀው የሚያስጠነቅቁት ከስድስቱ መስፈርቶች አንደኛው ከጎደለ አንድ ማህበረሰብ በፍጹም ብሔር ሊባል እንደማይችል ነው።

ከዚህ በመነሳት በትክክል በኢትዮጵያ ብሔር ሊባል የሚችል ጎሳ ማግኘት ይቻላል ወይ? ከተባለ መልሱ በፍጹም ይሆናል። በአንጻሩ ማርክሲስቶች እና ኢምፔሪያሊስቶች ባስቀመጧቸው መስፈርቶች ከተመዘነ በሀገራችን ኢትዮጵያ ከሚባል ብሔር ውጭ ሌላ ብሔር እንደሌለ በጉልህ መገንዘብ ያስችለናል።

ይህን ስል ከጎሳ ፖለቲካ ውጭ ማየት የማይችሉ ዋልታ ረገጦች ጨፍላቂ ሊሉኝ እንደሚችሉ ቅንጣት ያህል ጥርጣሬ የለኝም። ምክንቱም ለእኛ ሀገር ፖለቲከኞች ብሔር ማለት ቋንቋ እና ጎሳ ብቻ ስለሚመስላቸው የሆነው ሆኖ ግን እኛ ኢትዮጵያዊያን ከማርክሲስቶች እና ከኢፔሪያሊስቶች የተዋስናቸውን ቃላት በቅጡ ሳንረዳ እና ሳንገነዘብ ብሔር ለሚለው ሰፊ ጽንሰ ሃሳብ “ቋንቋ እና ጎሳ” የሚል የራሳችንን የተዛባ ትርጓሜ ሰጥተን ከእኛ ውጭ ፖለቲካ ለአሳር በሚል ተኮፍሰን ራሳችንን እያሞኘን እንገኛለን።

ብሔር እና መሰል ሰፊ የፖለቲካ ጽንሰ ሃሳቦች በቅጡ ያልተረዱ ራሳቸውን በፖለቲከኞች ባቡር ያሳፈሩ ዲስኩራሞች ለበርካታ ዓመታት ተዋልዶ እና የተጋምዶ የኖረን የኢትዮጵያን ማህበረሰብ ለመለያየት የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ስመለከት የ1950ዎቹ እና 60ዎቹ ፖለቲከኞች የኢትዮጵያ የታሪክ ስብራቶች አድርጌ እንዳይ አስገድዶኛል።

በመጨረሻም ሳይቸግረን ከውጭ ሀገራት የምንቃርማቸውን የፖለቲካ ጽንሰ ሃሳቦች በቅጡ እንረዳ፤ የሀገራችንን አንድነት በማጠናከር ታሪካዊ ኃላፊነታችንን እንወጣ! መልዕክቴ ነው።

# በአዲስ አበባ 60 የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኃይል መሙያ ማሽኖች ተገጥመዋል

## - በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከ100 ሺህ ተሻግሯል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ 60 የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የኤሌክትሪክ ኃይል መሙያ ማሽኖች መገጠማቸውን የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር አስታወቀ። ከውጭ የገቡና በሀገር ውስጥ ተገጣጥመው አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከ100 ሺህ በላይ መድረሳቸው ተገልጿል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ በርኦ ሀሰን የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪን በተመለከተ በሰጡት ማብራሪያ፤በአዲስ አበባ ከተማ 60 የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ኃይል መሙያ ማሽኖች በተለያዩ አካባቢዎች መገጣጠማቸውን አስታውቀዋል።

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ባለቤቶች ከመኖሪያ ቤታቸው በተጨማሪ ልክ እንደማደያዎች ሁሉ ተሽከርካሪያቸውን የኤሌክትሪክ ኃይል የሚሞሉበትን አማራጭ ለመፍጠር በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ በአዲስ አበባ ብቻ በ10 ዓመት ውስጥ አንድ ሺህ 176 የኃይል መሙያዎችን ለመግጠም ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ቻርጅ መሙያ ማዕከላት ግንባታን ወደ ክልል ከተሞች የማስፋፋት ሥራና ረጅም ርቀት የሚጓዙ ተሽከርካሪዎችን ወደ ገበያ የማስገባት ሥራ ላይ በትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝም ጨምረው ገልጸዋል።

በሌሎች የሀገሪቷ ከተሞች የኤሌክትሪክ ኃይል መሙያ ማዕከላት ለማስፋፋት ከሚመለከታቸው ተቋማት፣ ድርጅቶችና ከግሉ ዘርፍ ጋር በማቀናጀት ማዕከላቱ የሚገነቡበት ቦታ እንዲያመቻቹ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ በርኦ፤ በ10 ዓመት እቅዱ ውስጥ ሁለት ሺህ 335 የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኃይል መሙያ ማዕከላት ይገነባል ብለዋል።

ሀገሪቱ በዓመት የምታወጣውን አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር የነዳጅ ወጪ ለመቀነስ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ተቀርጾው እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ አቶ በርኦ ገለጻ፤ መንግሥት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ላይ ባደረገው የቀረጥ ማበረታቻና ከለውጡ ወዲህ በርካታ ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር እየገቡ ነው። በአሁኑ ወቅት ከውጭ የገቡና በሀገር ውስጥ የተገጣጠሙ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከ100 ሺህ በላይ መድረሱን አስታውቀዋል።

መንግሥት ያደረገው የቀረጥ ማበረታቻ የባለሀብቱ ተነሳሽነትና የሀገሪቷን የታዳሽ ኃይል አቅርቦት ለማሳደግ እንዲሁም የአየር ብክለትን ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት ለመደገፍ እንደሚረዳም ተናግረዋል።

በ10 ዓመታት ውስጥ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ 148 ሺህ አነስተኛ ተሽከርካሪዎችንና 48 ሺህ 555 አውቶቡሶችን ወደ ሥራ ለማስገባት መታቀዱን አስታውሰው፤ በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ላይ የመንግሥት ቁርጠኛነት በመጨመሩ እና በሁለት ዓመት ውስጥ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከ100 ሺህ በማለፉ እቅዱን ለመከለስ ተገደናል ብለዋል።

በዚህም መሠረት በ10 ዓመት ውስጥ 439 ሺህ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች እንደሚኖሩ የተጠና ጥናት ያመላክታል። ለነዚህ ተሽከርካሪዎችም ሁለት ሺህ 335 የኃይል መሙያ ማዕከል ይኖራል። ይህን ዕቅድ ለማሳካት ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገራት ኩባንያዎች ጋር በጥምረት ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙ አስረድተዋል።

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የትራንስፖርት ዘርፉን ከነዳጅ ጥገኝነት በማላቀቅ ለነዳጅ ግዢ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ለመቀነስ ይረዳል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ዘርፉ በኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ ሚኒስቴሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ለግል ዘርፉ እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች ከኢኮኖሚ ጠቀሜታና ከአየር ብክለት መከላከል ባለፈ የድምጽ ብክለትን ለማስቀረትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠን የሚረዱ መሆናቸውን ሚኒስትር ዴኤታው ተናግረዋል።

# ኢንዱስትሪዎች በጋራ እንዲሠሩ ለማስቻል ስትራቴጂካዊ አጋርነት መፍጠር ተጀምሯል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ኢንዱስትሪዎች አብሮ በጋራ መሥራትን እና ምርት መቀባበልን እንዲላመዱ የሚያስችል ስትራቴጂካዊ አጋርነት ከክልሎችና ተቋማት ጋር መፍጠር መጀመሩ ተገለጸ፡፡

ኦ ፕሮድዩስ ኢንቨስትመንት ግሩፕ እና ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነት ትናንት ተፈራርመዋል፡፡

የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ሥራ አስፈጻሚ አምባሳደር ሱለይማን ደደፎ፤ ስምምነቱ አብሮ በጋራ መሥራትን፣ ምርት መቀባበልንና ምርምሮችን በጋራ መሥራት የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፤ ከሁሉም የክልል ተቋማት ጋር ስትራቴጂካዊ አጋርነትን መፍጠር ተገቢ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

የመግባቢያ ስምምነት ፊርማውም ኢንዱትሪዎች በጋራ እንዲሠሩ ለማስቻል ስትራቴጂካዊ አጋርነትን መፍጠር ለመጀመሩ ማሳያ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ በሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ዘርፉን መምራት፣ ማገዝና ማስፋፋት ላይ እየተሠራ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ አምራችነትን በማስፋፋት፣ ከውጭ የሚገባን ምርት በመቀነስ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡትን መደገፍ ይገባል ብለዋል፡፡

ኦ ፕሮድዩስ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ሥራ አስፈጻሚ ኢንጂነር ማርታ በላይ በበኩላቸው፤ ስምምነቱ በማሽን መለዋወጫ፣ ዕቃ አቅርቦትን ጨምሮ በቴክኖሎጂ ውጤቶች ትግበራና በቴክኒካል እገዛ ዘርፍ በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

ግሩፑ ለክልሉ ብሎም ለሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል ያሉት ኢንጂነር ማርታ፤ የመንግሥት ሀብት የሆኑ የልማት ድርጅቶችን በገበያ ሥርዓት ውስጥ ተወዳዳሪና ውጤታማ ለማድረግ እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሬን ለማዳን በመስራት ላይ እንደሚገኝም ነው የጠቆሙት፡፡

የተለያዩ የማሽን መለዋወጫዎችን እቃዎችንና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት እየተሰራ መሆኑን በመግለጽ፤ በማሽን መዋወጫ እጥረት ምክንያት የሚፈጠሩ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ እንደሚያስችል አመልክተዋል፡፡

ኦ ፕሮዲዩስ ግሩፕ በገበያ ሰንሰለቱ ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት፣ ዋጋን ለማረጋጋትና የክልሉን ኅብረተሰብ ተጠቃሚ ለማድረግ እንደሚሠራም አያይዘው ተናግረዋል፡፡

አቅምን አሟጦ በመጠቀም ሀገሪቱ ወደ ኢንዱስትራላይዜሽን ለምታደርገው ጉዞ የበኩሉን ለመወጣት የተቋቋመ ግሩፕ ነው ያሉት ኢንጂነር ማርታ፤ በስሩ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎች የልህቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሆነው እንዲያገለግሉ እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

ኦ ፕሮድዩስ ኢንቨስትመንት ግሩፕ የኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ግሩፕ አካልና የመንግሥት የልማት ድርጅት ሲሆን፤ ስድስት ኢንዱስትሪዎችን እያስተዳደረ የሚገኝ መሆኑ ተገልጿል፡፡

# ታንዛኒያ የኤሌክትሪክ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በመቶ እንደማይበልጥ መረጃዎች ያመለክታሉ ያሉት አምባሳደሩ፤ ይህንን የኃይል ክፍተት ለመሙላት ከቀጣናው ሀገራት ታዳሽ የኤሌክትሪክ ኃይል መግዛትን እንደ አማራጭ ይዛለች፤ በዋናነት ኢትዮጵያ ከታንዛኒያ ጋር የተፈራረመችው የኤሌክትሪክ ኃይል ንግድ የመግባቢያ ሰነድ በአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ማዕቀፍ ስር በመሆኑ ከታንዛኒያ አልፎ አህጉራዊ ትስስርና ትብብርን ለመፍጠር የጎላ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ገልጸዋል።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ በቅርቡ በኢትዮጵያና በታንዛኒያ መካከል የተደረገው የ400 ኪሎ ቦልት የኃይል ሽያጭ ስምምነት የመጀመሪያው ምዕራፍ ነው የሚል እምነት አለን። ስምምነቱ ተፈጻሚ ከሆነ በኋላ ተጨማሪ የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ስምምነቶች ይደረጋሉ። ይህን ለማድረግ በሁለቱም ሀገራት በኩል ፍላጎቶች አሉ።

በኢትዮጵያ በኩል የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ስምምነት ተፈጻሚ እንዲሆን በትኩረት መስራት ተገቢ መሆኑን አመልክተው፤ በአፈጻጸሙ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ የቴክኒክ ችግሮች ካሉ በውይይት መፍታት የሚቻልበት አሠራር እንዲዘረጋ በትጋት እንደሚሠራ ገልጸዋል።

ታንዛኒያ ያላት አጠቃላይ የኃይል መጠን አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ 38 ሜጋ ዋት ገደማ ሲሆን ከ60 በመቶ በላይ የምታገኘው ከተፈጥሮ ጋዝ ነው። በመገንባት ላይ ያለው የጁሊዬስ ኔሬሬ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድብ ሁለት ሺህ 115 ሜጋ ዋት ኃይል ያመነጫል ተብሎ ይጠበቃል። ሲጠናቀቅ አጠቃላይ የሀገሪቱ የኤሌክትሪክ ኃይል አራት ሺህ ሜጋ ዋት ይጠጋል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል አምባሳደሩ።

ሁለቱ ሀገራት ታሪካዊ ግንኙነት የጀመሩት እኤአ በ1960ዎቹ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ ሁለቱን ሀገራት በባህል፣ በታሪክ፣ ኢኮኖሚ ጠንካራ ትስስር አላቸው። ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2018 ጀምሮ ኤምባሲዋን በመክፈት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቱን ለማጠናከር እየሠራች እንደምትገኝ ገልጸዋል።

# የሀገር ውስጥ ምርቶችን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የምጣኔ ሀብት ምሁር የሆኑት አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ፤ ተቋማት የሀገር ውስጥ ምርቶች እንዲገዙ አስገዳጅ ሁኔታ መፈጠሩ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል።

የመጀመሪያው የሀገር ውስጥ አምራቾችን በማበረታታት ተወዳዳሪ የሆነ ምርት ይዘው እንዲቀርቡ የሚያደርግ ሲሆን፤ ሌላኛው ሀገሪቱ ከውጪ የምታስገባቸውን ምርቶች በመቀነስ የምታወጣውን የውጪ ምንዛሬ እንድትቆጥብ ይረዳታል።

በአንድ ሀገር እንዲህ አይነት ውሳኔዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ሲታሰብ ሰፊ ሥራዎችም አብረው መሠራት ይኖርባቸዋል ያሉት አቶ ዘመዴነህ፤ በኢትዮጵያ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የሀገር ውስጥ ምርት አቅራቢዎች ያሉባቸውን ችግሮች መቅረፍ ያስፈልጋል ብለዋል። በዋናነትም ከውጪ የሚገቡ ግብዓቶችን በተለይም መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ የማሟላት ሥራ ይጠበቃል ሲሉ ይናገራሉ ።

ሌላኛው ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ እክል የሚሆነው ሃገር ውስጥ ያሉ አምራቾች በቂና ጥራት ያለው ምርት ማቅረብ ይችላሉ ወይ የሚለው ነው የሚሉት አቶ ዘመዴነህ፤ በሃገር ውስጥ የሚመረቱ መኪናዎችን ውስንነት ለአብነት መጥቀስ ይቻላል ሲሉ ይገልጻሉ።

ዓለም ላይ ባለው ተሞክሮ እያንዳንዱ እቃ በብዛት ሲመረት የምርቱ ዋጋ እየቀነሰ ይመጣል። በዚህም የሀገር ውስጥ አምራቾች የሚመረቱ ምርቶችን በብዛትና በጥራት እንዲያመርቱ መንግሥት አስፈላጊውን ርብርብ ማድረግ ይኖርበታል ይላሉ።

ማህበረሰቡ የሀገር ውስጥ ምርት የመጠቀም ፍላጎቱ አናሳ ነው ያሉት አቶ ዘመዴነህ በተለይም አልባሳት ላይ ሰፊ ክፍተት አለ። ይንን መቅረፍ የሚቻለው ጥራት ያላቸውን ምርቶች ከማምረት ባለፈ ተቋማት ላይ የተላለፈውን አስገዳጅ ውሳኔ በማህበረሰቡ ላይም ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ ያስረዳሉ። የሀገር ውስጥ ምርትን መግዛት ምርጫ ብቻ ሳይሆን ግዴታ መሆን ይኖርበታል ሲሉም ያክላሉ።

ሌላኛው በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ የሰጡት የምጣኔ ሀብት ምሁር ዶክተር ይንገስ አለሙ በበኩላቸው፤ ያደጉ ሀገራት ኢኮኖሚያቸው አሁን ያለበት ደረጃ እንዲደርስ ካደረጋቸው ምክንያቶች አንዱ ራሳቸው የሚያመርቷቸውን ምርቶችም ሆነ የሚፈጥሯቸውን የቴክኖሎጂ ግኝቶች ቅድሚያ በሀገር ውስጥ መጠቀማቸው ነው።

እነዚህ ያደጉ ሀገራት ማህበረሰባቸው ለሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ግንዛቤ ከማሳደግ ባሻገር ሕጎችንም በማውጣት ተግባራዊ ሲያደርጉ ቆይተዋል ይላሉ።

በሀገራችንም ይህ ውሳኔ መተላለፉ የሀገር ኢኮኖሚ እንዲዳብር ፣የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ እንዲሰለጥን እንዲሁም የሀገር ውስጥ አምራቾች እንዲበረታቱ የሚያደርግ ነው ሲሉ ይገልጻሉ።

አንድ ሀገር የአግሮ ኢንዱስትሪ እና የኢንዱስትሪ ዘርፉን ቀጣይነት ባለው መልኩ አቅም ማሳደግ ከቻለች እና ለሀገር ውስጥ ምርት ቅድሚያ ሰጥታ የምትሠራ ከሆነ የዋጋ ንረቱንም ሆነ የምርት እጥረትን መቆጣጠር ያስችላታል ያሉት ዶክተር ይንገስ፤ ይህን ውሳኔም ውሳኔው ማህበረሰቡ ላይ ተግባራዊ በማድረግ አሁን ላይ በምዕራባውያን ሥራ ያለ የሚመስለውን የአመጋገብ እና የአለባበስ ሥርዓታችንን መመለስ እንችላለን ሲሉ ያብራራሉ።

ምሁራኑ እንደገለጹት፤ ለሀገር ውስጥ ምርት ቅድሚያ መስጠት በአንድ በኩል አምራቹ እንዲበረታታ በማድረግ የምርት እድገት እንዲጨምር የሚያደርግ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በመተካት የውጭ ምንዛሪ ወጪን መቀነስ ያስችላል። ይህ ደግሞ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትን ለማረጋገጥ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል።

# ወቅታዊ

# “ወደ 71 የሚሆኑ የእንስት ዝርያዎች እንዳይጠፉ አድርገናል”

**ዶክተር ዮሐንስ ገብሩ**
**የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚዳንት**


ፎቶ፡- ሃዲስ አብርሃ

አስቴር ኤልያስ

**ዩኒቨርሲቲዎች ከሚኖራቸው ዓለም አቀፋዊ፣ ሀገራዊና ክልላዊ ጠቀሜታ አኳያ በሶስት ዋና ዋና ተልዕኮዎች የተለዩ መሆናቸው ይታወቃል። ይኸውም የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች፣ አፕላይድ (የትግበራ) ሳይንስ ዩኒቨርሲቲዎች እና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች በሚል ነው። በአራተኝነት የተቀመጡት ደግሞ አጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዎች ሲሆኑ፣ አንድ ተጨማሪ ልዩ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ (ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ) መለየቱን የትምህርት ሚኒስቴር ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።**

**በአፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲዎች ከተካተቱ 15 ዩኒቨርሲቲዎች መካከል አንዱ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ሲሆን፣ አፕላይድ ሳይንስ ሲባልም በተጨባጭ ጥናታዊ ትግበራ ላይ በመመሥረት የተጠቃለሉ ትምህርቶችን የሚያቀርብ ዘርፍ መሆኑ ይነገራል። ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኞች ቡድን በመስክ ሥራው ወደ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በማቅናት ከዩኒቨርሲቲው የምርምር፣ የማኅበረሰብ አገልግሎትና የቴክኖሎጂ ትራንስፈር ምክትል ፕሬዚዳንት ከሆኑት ከዶክተር ዮሐንስ ገብሩ ጋር በዩኒቨርሲቲው እየተካሔዱ ስላሉ የማኅበረሰብ አቀፍ አገልግሎት እና የምርምር ሥራዎችን እንዲሁም ስለ አፕላይድ ሳይንሱ ሁኔታ ሳይና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ትኩረት አድርጎ ተከታዩን ዘገባ አጠናቅሯል።**

**አዲስ ዘመን፡- ዩኒቨርሲቲው በማኅበረሰብ አቀፍ አገልግሎት እና በምርምር ሥራዎች ትኩረት አድርጎ የሚሰራው በየትኞቹ ላይ ነው?**

**ዮሐንስ (ዶ/ር)፡-** ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በምርምር የማኅበረሰብ አገልግሎት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። ከምንሠራቸው በርካታ ምርምሮች ለምሳሌ ያህል እኤአ ከ2021 እስከ 2022 ድረስ ወደ 50 ፕሮጀክቶች ነበሩ። ሶስት ደግሞ ሜጋ ፕሮጀክቶች ነበሩ። እኤአ በ2023 ደግሞ ወደ 48 ፕሮጀክቶች ነበሩ። እነዚህን ፕሮጀክቶች የምንሰራው ከምርምር ጎን ነው።

ፕሮጀክቶቹን የምናስኬዳቸው ከመንግሥት ከሚመደብልን በጀት በተጨማሪ ከተለያዩ ድርጅቶች ከምናገኘው በጀት ነው። በዘንድሮ ዓመትም ይህን እየከለስን ነው። ሰሞኑን ለመምህራን በተመረጡ የምርምር መስኮች ላይ ድጋፍ መስጠት እንጀምራለን።

ወደ ማኅበረሰብ አገልግሎት ስንሄድ በዚህ አገልግሎት የምንሰራው በተለያዩ ዘርፎች ነው። በዋነኝነት በትምህርት፣ በጤና እና በኢነርጂ ላይ ትኩረት አድርገን እየሠራን እንገኛለን። ከባለፈው ዓመት ጀምሮ በተለይ የትምህርት ሥርዓቱ ያጋጠመውን ችግር ለመቅረፍ መምህራኑ በ20 ትምህርት ቤቶች በምስራቅ ጉራጌ ዞንና በሁለት ልዩ ወረዳዎች በመጓዝ ቅዳሜ ቅዳሜ የማጠናከሪያ ትምህርት እየሰጡ ነው።

በተጨማሪም በጤና ዘርፉ ላይ ደግሞ በአካባቢያችን የሚገኙ የሕክምና ተቋማትን የማጠናከር ሥራ እንሠራለን። በቅርቡም በዩኒቨርሲቲያችን አጠገብ ሐዋሪያት የሚባል ሆስፒታል የማስጀመር እንቅስቃሴ እያደረግን ነው።

በግብርናው ዘርፍ ሰርቶ ማሳያዎች አሉን። የፈርዝዬ የእንሰት ምርምር ማዕከል አለን። ይህ ማዕከል በእንሰት ዙሪያ የሚሰራ ነው ሲሆን፣ ይህ የምርምር ጣቢያ ከዩኒቨርሲቲያችን 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ነው። ምቄ የሚባል ጣቢያ አለን፤ እዛ ደግሞ የቡና እና የፍራፍሬ ምርምር የሚካሔድበት ጣቢያ ነው። ሌሎችም የምርምር ጣቢያዎች ያሉን ሲሆን፣ በዋነኝነት ግን ሁለቱ ጣቢያዎች በርካታ ሥራዎች የሚሰሩባቸው ናቸው።

ከቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር ተያይዞም ተመሳሳይ ሥራዎችን እንሰራለን። የአይ.ሲ.ቲ ኢንኩቤሽን ማዕከል አለን። ከኢንጂነሪንግ መምህራን ጋር የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን እንሠራለን። ለሀገር መትረፍ የሚችሉ ወጣት ልጆች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጥተው የሚሰለጥኑበት እና አቅማቸውን የሚያሳድጉበትን ሁኔታ እየፈጠርን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የዩኒቨርሲቲው መምህራን በሃያ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን እየረዱ ነው ብለዋልና እየተረዱ ያሉት ምን ያህል ተማሪዎች ናቸው? አጋዥ ናቸው የሚባሉትስ መምህራን ቁጥር ምን ያህል ነው?**

**ዮሐንስ (ዶ/ር)፡-** ዘንድሮ እየጀመርን ስለሆነ ልገልጽ የምችለው የአምናውን ነው። በዚህ ሲሳተፉ የነበሩት እስከ ስድስት ሺ የሚደርሱ ማለትም አምስት ሺ 885 አካባቢ ተማሪዎች ናቸው። ለማብቃት ጥረት እያደረግን ያለው ከዘጠነኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉትን ተማሪዎች ነው።

እንደሚታወቀው የትምህርት ጥራት ለውጡን በአንድ ጊዜ ማምጣት የሚቻል አይደለም። ይሁንና ባገኘነው ግብረመልስ ብዙዎች እየተጠቀሙበት ነው። ወደ ሃያ ትምህርት ቤቶች እንሂድ እንጂ ሥልጠናውን የሚሰጡት የእኛ መምህራን ብቻ አይደሉም። በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ እኛ መድረስ የምንችልበት አይደለም። በጠዋት መድረስ የሚችሉትን ከእኛ ወደ 50 መምህራንን እንጠቀማለን። አገልግሎቱን ስንሰጥ የቆየነው 50 መምህራን ደግሞ ሁለተኛ ዲግሪና ከዚያ በላይ ያላቸውን ከዞኑ የተመረጡ መምህራንን እየተጠቀምን ነው። ከዚህ የተነሳ ተሳታፊ የሆነው ወደ መቶ መምህር ነው ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ከመምህራኑ የሚጠበቀው ምን ዓይነት አሰራር ነው? ቀጥታ ሔደው ማስተማር ብቻ ነው? ወይስ ሌላ ተጨማሪ የሚያደርጉት ሥራ አለ?**

**ዮሐንስ (ዶ/ር)፡-** መምህራኑ የሚያስተምሩት የማጠናከሪያ ትምህርት ነው። በተለይ ደግሞ ወደ ገጠር ወጣ ሲባል አንዳንዶቹ ትምህርት ቤቶች በቂ መምህራን የሌላቸው ናቸው። ወይም ደግሞ አንዱን የትምህርት ዓይነት በትክክል ለዛ ተብሎ የዘርፉ መምህር ሳይሆን የሚያስተምረው ሌላ የትምህርት ዘርፍ ላይ ያለ መምህር ነው። እንደዚህ ዓይነቱን ክፍተት ለመሙላት ሙከራ እናደርጋለን። እንዲያም ሆኖ ትክክለኛውም መምህር ቢኖርም ተጨማሪ እውቀት ለመስጠት እናስተምራለን።

ከዚህ ጋር አያይዤ መጥቀስ የምፈልገው ነገር ቢኖር የመምህራን አቅም ከማጎልበት አንጻር ሰሞኑን የጨረስነው ከአንድ ሺ አንድ መቶ በላይ መምህራንን የዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ድረስ በመጥራት የአምስት ቀን ሥልጠና ሰጥተናል። ይህንን ሥልጠና የሰጠነው በቅርቡ ከተዋቀረው አዲሱ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጋር በመተባበር ሶስት የኒቨርሲቲዎች ነን። ይህ ማለት ጉራጌ ዞን ላይ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ዞኖች ላይም የተካሔደ ነው። ለምሳሌ የም ዞን የሚባል አለ። የሰጠነው እርሱንም ዞን ጨምረን ነው። ወራቤም ዋቸሞም ዩኒቨርሲቲ በተመሳሳይ ሰጥቷል። በዚህ መልኩ ሶስት የኒቨርሲቲዎች ተቀናጅተን ክልሉ ላይ ያሉ መምህራንን የአዲሱ የሥርዓተ ትምህርት የመጽሐፍ ማስተዋወቂያ ባለፈው ወር አጠናቅቀናል።

**አዲስ ዘመን፡- ከእንሰት ምርት ምርምር ጋር ተያይዞ ምን የተሠራ ነገር አለ? የአካባቢው ኅብረተሰብ ከምርቱ በአግባቡ እንዲጠቀምስ ምን ታስቧል።**

**ዮሐንስ (ዶ/ር)፡-** ከእንሰት ጋር ተያይዞ እየሠራን ያለነው በሶስት ጉዳዮች ላይ አተኩረን ነው። አንደኛ ምርቱ እንዳይጠፋ ማድረግ ነው፤ ምክንያቱም እንሰት የተለያየ ዝርያ ያለው እንጂ ዝርያው አንድ ዓይነት አይደለም። እኛ ባለን የፈርዝዬ ማዕከል ያሉን የእንሰት ዝርያዎች ወደ 71 ያህል ናቸው። እያንዳንዱ ዝርያ የራሱ ጥቅም አለው። የሚያድግበት የአየር ጸባይም አለ። ስለዚህ ወደ 71 የሚሆኑ የእንሰት ዝርያዎችን እንዳይጠፉ ማድረግ ችለናል።

አንዳንዶቹ ዝርያዎቹ ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉ ስለነበሩ ከአርሶ አደሩ ማሳ ቀስ በቀስ እየተመናመኑና እየጠፉ የመጡ ስለሆነ እኛ እንዳይጠፉ በማድረግ ባለፈው ዓመት መልሰን በባዮ ቴክኖሎጂ ደግሞ በቲሹ ካልቸር አባዝተን ስንሰራ ቆይተናል። ስለዚህ ወደ ፈርዝዬ የእንሰት ምርምር ማዕከል የሄደ አንድ ሰው የሚያየው ነገር እንዳይጠፉ የምናደርግበት በብሎክ የተከፋፈለ ለእይታ አንድ ዓይነት የሚመስል ሊሆን ይችላል እንጂ በዝርያ ሲጤን ወደ 71 አንድ ዓይነት ዝርያን ማየት ይቻላል።

ሌላው ከእንሰት ጋር ተያይዞ ሁለተኛው ሥራችን በሽታን የመከላከል ሒደት ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ በጣም ደስ የሚል ዜና ተገኝቷል። እንሰት ላይ ከተጋረጡ በርካታ ጉዳቶች አንዱ በሽታ ነው። ባክቴሪያ ዊልት የሚባለው በአማርኛ ደግሞ “እንሰት አጠውልግ” የሚባል የበሽታ ዓይነት አለ። ይህ የበሽታ ዓይነት እንሰትን ከማሳ እያስወገደ ያስቸገረ ነው። ለአርሶ አደሩም ከባድ የሆነ ፈተና ነበር። ዩኒቨርሲቲያችን ከተቋቋመ 11 ዓመቱ ነውና እዛ ላይ በርካታ ምርምሮች ሲካሔድ ቆይቷል። ነገር ግን መጨረሻው ላይ ሳይደርስ ሌላ ዩኒቨርሲቲ አግኝቷል። እሱ ደግሞ ድካማችንን የሚያቀል ነገር ነው። ስለዚህ ምርምሩ አንዱ የሚያተኩረው እሱ ላይ ነው ማለት ነው።

ሌላው ደግሞ በዋነኝነትና በጣም ወሳኝ የሆነው ሒደቱ ነው። እንሰት በእናቶች አቅም የሚሰራ በመሆኑ በጣም አድካሚ ነው። እናቶች በዚህ ሥራ በጣም ይደክማሉ። ስለዚህ እሱን ለመቅረፍ አሁንም በተለያዩ ተቋማት የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ይታያል፤ በተለይ ማሽነሪ ለማምረት ጥረት ተደርጓል። በእኛም ተቋም ሁለት ማሽኖች ፈጥረን እና ድጋፍ አግኝተን በቅርቡ ሰርቶ ማሳያ ላይ ሙከራ አድርገናል።

የባዮ ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ባለበት መድረክ ወልቂጤ ላይ ማሽኖች ተሻሽለውና ያሉባቸው ጥቃቅን ችግሮች ከተፈቱ ያቀድነው ለእያንዳንዱ አርሶ አደር እንኳ ማድረስ ባንችል በጋራ የተደራጁ ወጣቶችን በማዋቀር ልክ እንደ እንሰት ወፍጮ ቤት ዓይነት ነገር በወረዳው ላይ ለማቋቋም ነው። ይህን አስፍቶ ከመሥራት አንጻር አሁንም ድጋፍ እየፈለግን ነው። ጥሩ ደረጃ ላይ ደርሰናል። የተወሰነ ድጋፍ ካገኘን የምናሰፋበት ሁኔታ ይፈጠራል።

ሌላው ከምርምር ጋር ወደ አራት ፕሮጀክቶች አሉ። አንዱ ሜጋ ፕሮጀክት ነው። ባዮ ስለሪ (ከባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ የሚገኝ የተፈጥሮ ማዳበሪያ) ወይም ከከብቶች የሚገኝ ፈሳሽ ሲሆን፣ እሱ በእንሰት ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ምንድን ነው? የሚል ግምገማ እየተሠራ ነው። ከዚህ አንጻር የተፈጥሮ ማዳበሪያን ከመተካት አኳያ ትልቅ ፋይዳ ያለውን ተግባር እያከናወንን እንገኛለን።

ከሙዝ ጁስ ጋር በተያያዘ እንሰት ምን ያህል ጠቀሜታ አለው የሚለውን በማየቱ በኩል የምግብ ሳይንስ ኢንጂነሪንግ በኩል አንድ ፕሮጀክት እየተሠራ ነው።

ሌላው የእንሰት ተረፈ ምርት ከአሸዋ እና ከጠጠር ጋር ተደበላልቆ ለአስፓልት ጥሩ ጥንካሬ ይሰጣል የሚል ጉዳይ ስላለ በሲቪል ኢንጂነሪንግ በኩል ምርምር እየተደረገበት ነው። ስለዚህ እንሰት የማይገባበት ቦታ የለም ማለት የሚያስችል ነው።

ከዚህ በተጨማሪ እንሰት የአየር ንብረት ተጽዕኖ እና የምግብ ዋስትና ላይ ያለው ሁኔታ ምንድን ነው? ለሚለው በአግሪካልቸር ኢኮኖሚክስ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች አሉ። ከእነዚህ አራት ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ በጣም ትልቅ ሜጋ ፕሮጀክት ነው። እሱም እስቀድሜ ባዮ ስለሪ ያልኩት ሲሆን፣ ይህ ትልቅ ፕሮጀክት በሶስት ዓመት ውስጥ የሚጠናቀቅ ነው። ሌሎቹ ግን ትንንሽ ቢሆኑም እንሰት ላይ አተኩረን ከምንሰራባቸው ምርምሮች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- የምርምር ስራችሁን ምን ያህል እያሰፋችሁት ነው? ለምርምር ስራችሁ ምን ያህልስ በጀት አላችሁ?**

**ዮሐንስ (ዶ/ር)፡-** ትኩረት የምናደርገው እንሰት ላይ ነው። አንደኛ ዩኒቨርሲቲያችንም የሚገኝበት ማኅብረሰብ በእንሰት አብቃይነቱም ተጠቃሚነቱም የሚታወቅ ነው። ስለዚህ እኛ የተለየ ኃላፊነት አለብን ብለን እናምናለን። ለምሳሌ የፈርዝዬ ማዕከላችን ላይ እንዳይጠፉ የታደግናቸው (ዝሪያቸውን ያሻሻልንበት) በፊት የነበሩ ወደ 57 ዝርያዎች ነበሩ። አሁን በአዲሱ በተሻሻለው ወደ 71 አሳድገነዋል። የመጀመሪያውን ዝርያ

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ወቅታዊ

## “ወደ 71 የሚሆኑ የእንሰት ዝርያዎች...

ከገጽ 7 የዞረ



የምናሻሽልበት ጣቢያ ወደ ስምንት ዓመት ስለሆነው የሚተካ ነው። ከዚህ አንጻር የመተካት ሥራዎችንም ሰርተናል።

“ኮል ፎር እንሰት” በሚል ለብቻ ያወጣነው የምርምር ጥሪ ነበር። “ኮል ፎር እንሰት” ስንል የእኛ ተቋም ተመራማሪዎች ከሌላ ተቋም ተመራማሪዎች ጋር ተቀናጅተው ምርምር የሚሰሩበትን እድል ነው የፈጠረ ነው። ስለዚህ እዚህ ብቻ የሚታጠር ሳይሆን እንደ ሀገር አቅም አለን፤ እንሰት ዙሪያ እንሥራለን የሚሉ አቅም ያላቸውን አካላት ጋብዘናል። ነገር ግን ያለቀው ገና ፕሮፖዛሉ ነው። የርዳታ ስምምነት ተፈራርመናል። ከዚህ አንጻር እኛ እድሉን ፈጥረናል። እየሰራን ያለነው በእንሰት ዙሪያ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በርከት ያሉ የእንሰት ዝርያዎችን በማሻሻል ሳይ ናችሁ፤ ይህ ዝርያ ወደአርሶ አደሩ ይደርሳል? አገልግሎቱስ ለምግብነት ብቻ ነው?**

**ዮሐንስ (ዶ/ር)፡-** የእንሰት እያንዳንዱ ዝርያ የራሱ የሆነ ልዩ ባህሪ አለው። አንዳንዱ ለምግብነት የሚውል ሲሆን፣ አንዳንዱ ደግሞ ለመድኃኒትነት የሚውል ነው። ቀደም ባለው ጊዜ በተለይ ስብራት ያጋጠመው ሰው ሊጠግነው የሚችል አንደኛው የእንሰት ዓይነት መኖሩ ይታወቃል። ይሁንና ሁሉም የእንሰት ዓይነት ይህን ዓይነት መድኃኒትነት ይሰጣል ማለት ግን አይደለም። በተለምዶ እኛ እንሰት እንላለን እንጂ የሚያውቁ ሰዎች የጠጋኝነት ሚና የሚጫወተውን የእንሰት ዓይነት ስብራት ላጋጠመው ሰው ይሰጡታል።

እንሰት ምግብ ብቻ አይደለም፤ መተኛም ጭምር እንጂ። ለምሳሌ “ጅባ” በሚል መጠሪያ የሚታወቀው ከእንሰት ምርት የሚዘጋጀው ለመኝታ አገልግሎት የሚውል ነው። ከእንሰት ተረፈ ምርት መተኛ የሚሆን አልጋ ነገር ይሰራል። አሁን አሁን የእንሰት ተረፈ ምርት ወረቀት እየሆነ እንደሆነ እየተነገረ ነው። በአሁኑ ወቅት በጣም ጠንካራ እና ጥሩ የሚባል የወረቀት ዓይነት ወጥቶታል።

ስለዚህ እንሰት አንደኛ የአየር ጸባይን ተከትሎ የሚመጣን ድርቅ የመቋቋም ብቃት ያለው ተክል ነው። ለምሳሌ ቀደም ባሉ ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ በተከሰቱ ድርቆች እንሰት አብቃይ የሆኑ አካባቢዎች ብዙ እንዳልተጎዱ ይታወቃል። ስለዚህ ይህ ድርቅ የሚቋቋም ተክል በኢትዮጵያ ለተክሉ ተስማሚ የአየር ጸባይ ባለበት ሁሉ ቢስፋፋ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ሚናው የጎላ ነው ብዬ አስባለሁ። ከዚህ ከምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

በርግጥ እንሰት አብቃይ ከሆኑ አካባቢዎች ውጭ እንሰት አይበቅልም ማለት አይደለም። ተክሉ ያለው አገልግሎትና ልምዱ ስለሌለ ነው እንጂ እንሰት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ተክል ነው፤ ከዚህ አንጻር በዘርፉ እየተሠራ በመሆኑ ወዳልተለመዱ አካባቢዎችም ተክሉ የተለያዩ ምርምሮች እየተካሔደባቸው እንዲስፋፉ እየተደረጉ ናቸው። ይህ መሆኑ ደግሞ እንሰት ጠቀሜታው ከፍ እንዲል የሚያደርጉ ናቸው።

በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባን ጨምሮ በዋና ዋና ከተሞች እንሰት በጣም ውድ እየሆነ ነው። ምክንያቱም እንሰት ከገጠር ምግብነት ወደ ከተማ ምግብነት እየመጣ በመሆኑ ነው። ለምሳሌ ቆጮ አንዱ ነው። ስለዚህ እኔ የማስበው ትልቅ ትኩረት የሚሻ ተክል ነው ብዬ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ወደአፕላይድ ሳይንስ (ተግባር ተኮር ሳይንስ) የሚደረገው ጉዞ ምን ይመስላል?**

**ዮሐንስ (ዶ/ር)፡-** እኛ የአፕላይድ ሳይንስ እጩዎች ነን። እንዲህም ስል ባለን አቅጣጫ አፕላይድ ሳይንስ ውስጥ ገብተናል። አፕላይድ ሳይንስ ውስጥ ከገቡ የሶስተኛ ትውልድ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ነን። እሱ ሲታይ ደግሞ እዛ ውስጥ እንድንመደብ ያደረገን አንዱ ቤተ-ሙከራችን (ላቦራቶሪያችን) ነው። ሌላው የማስበው የሠራተኛው መገለጫ (የስታፍ ፕሮፋይላችንም) ጥሩ ነው ብዬ ነው። መልክዓ ምድራዊ (የጂኦግራፊካል) ሁኔታችንም የሰጠን ነገር ይኖራል የሚል እምነት አለኝ።

በዩኒቨርሲቲያችን ያለው ስታፍ ብዙ ነው። በሶስተኛ ዲግሪ ደረጃ በርካታ መምህራን አሉን። በላቦራቶሪዎቻችን ደግሞ ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች መጥተው የሚጠቀሙባቸው ናቸው። ሌላው ቀርቶ ከእኛ ቀደምት ናቸው ከሚባሉ ዩኒቨርሲቲዎች ጭምር ወደእኛ መጥተው በላቦራቶሪው የሚጠቀሙ አሉ። ከዚህ የተነሳ በአሁኑ ወቅት በተሟላ መልኩ ወደ ሙሉ አፕላይድ ሳይንስ ለመግባት በርካታ ሥራዎችን እየሠራን ነው። ከእነዚህ መካከል አንደኛው ነገር ስትራቴጂ እየነደፍን መሆናችን ነው። ሁለተኛው ደግሞ የትግበራ ስልት በኮሚቴ እየሠራን ነው። ከዚያ በኋላ ሥርዓተ ትምህርታችንን መከለስ ጀምረናል። ምርምሮቻችንን፣ የማኅበረሰብ አገልግሎቶቻችን አፕላይድ አፕላይድ የሚሸቱ ለማድረግ ጥረት እያደረግን ነው። ስለዚህ እነርሱን እንደ እዛ ለማድረግ በመጀመሪያ የሰነድ ዝግጅት እየጨረስን ነው። ስለዚህ በ2017 ዓ.ም ላይ በተሟላ ደረጃ እዛ ውስጥ እንገባለን ብለን ተስፋ እንደርጋለን። እስካሁንም ያንን ለማሟላት ሥራዎች እየተሰሩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ወደ አፕላይድ ሳይንስ ሙሉ ለሙሉ ለመግባት ከዩኒቨርሲቲያችሁ የሚጠበቀው ምንድን ነው?**

**ዮሐንስ (ዶ/ር)፡-** ከእኛ የሚጠበቀው የቴክኖሎጂ ሽግግር ሲሆን፣ እሱ በጣም ወሳኝ ነው። እኔ የምገለጸው ከማኅበረሰብ አገልግሎት አንጻር ነው። ያለሁበትም ቢሮ እሱ ስለሆነ ነው። ከማኅበረሰብ አገልግሎት አንጻር የሚካሔዱት አፕላይድ የሚመስሉ ምርምሮች ናቸው። እንደዛ ሲባል እውቀትን መሠረት ያደረጉ ምርምሮች አያስፈልጉም ማለት አይደለም። ነገር ግን ይበልጥ ትኩረታችን የሚሆነው ወደፈጠራውና ወደተግባሩ ነው።

**የእንሰት ተረፈ ምርት ከአሸዋ እና ከጠጠር ጋር ተደበላልቆ ለአስፓልት ጥሩ ጥንካሬ ይሰጣል የሚል ጉዳይ ስላለ በሲቪል ኢንጂነሪንግ በኩል ምርምር እየተደረገበት ነው**

በመማር ማስተማሩ ዘርፍ ደግሞ የምናበቃቸው ተማሪዎቻችን የተግባር ተማሪዎች ናቸው። ምርምር መሥራት የሚችሉ፤ ግን ምርምራቸው በተግባር የሚገለጥ ነው መሆን ያለበት። የመጨረሻው ውጤቱ እሱ ነው። ከአፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲዎች የሚጠበቀው ይኸው ነው እንጂ በተለመደው መልኩ ቲዎሪውን ብቻ አጣጥሞ እጁ የማይሰራ ተማሪ ሆኖ እንዲወጣ አይደለም።

ስለዚህ በተግባር ስልጡን የሆኑ ተማሪዎች ለማድረግ አንደኛ ወርክሾፖቻችን በጣም ማጠናከር አለብን። እሱ ላይ ደግሞ እየሠራን እንገኛለን። ምርምር ጣቢያዎቻችንን በጣም እያጠናከርን ነው። ከዚህ የተነሳ ጥሩ ደረጃ ላይ እንደርሳለን ብዬ እኔም ተስፋ አደርጋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ቀደም ብለው በቡና እና በፍራፍሬ ሳይም ምርምር እያካሔዳችሁ እንደሆነ ጠቅም አድርገዋል፤ ስለዚህ ጉዳይ ቢያብራሩልን ?**

**ዮሐንስ (ዶ/ር)፡-** ከቡና አንጻር ጅማ የቡና ምርምር ኢንስቲትዩት አለ፤ ከእነርሱ ጋር በጋራ ቢሆንም ወደ ስምንት ዓመታት ያስቆጠረና እየሰራንበት ያለ የምርምር ማዕከል አለ። ይህ የምርምር ሥራ የቡና ዝርያን ለማውጣት ነው። እሱ ሁለት ዓመት ነው የቀረው። በምርምር ቋንቋ የመጨረሻ መላመድ ሙከራ (አዳብቴሽን ቴስት) የሚባል አለ። እሱ ከተሠራ በኋላ ሊወጣ የሚችለው ዓይነት “የጉራጌ ቡና” የሚባለውን የተሻሻለ የቡና ዓይነት ሊሆን ይችላል። እኛ በዓለም አቀፍ ደረጃ የምናውቃቸው ዓይነት ስሞችን ለማውጣት ነው እቅዳችን።

ከፍራፍሬ አንጻር እየሠራን ያለነው አቮካዶ እና አፕል ላይ ነው። አንዱ ቡና ያለበት ቦታ ላይ አቮካዶን እየወሰድን ነው። ዋናው ማዘር ፕላንት የሚባል አለ። ብዙ ዓይነት ችግኞችን እያባዛን ለማኅበረሰቡ እንሰጣለን። ስለዚህ እያንዳንዱ ቡና ማብቀል የሚችል አርሶ አደር በጓሮው የአቮካዶና የአፕል ዝሪያዎችን እንዲያገኙ ጥረት እያደረግን ነው። ስለዚህ በዚህ ዓይነት ሁኔታ በየዓመቱ እናደርሳለን። ነገር ግን ያኛውን አሳፋፍተን መሄድ እንዳለብን እንገነዘባለን።

የቡናውን የጀመርነው ገና ባለፈው ዓመት ነው። ባለፈው ዓመት ወደ 27 ሺ የቡና ችግኞች ለአርሶ አደሮቻችን ሰጥተናል። ዘንድሮ ደግሞ አራት እጥፍ እናሳድጋለን ብለን አስበናል። ስለዚህ በዚህ ዓመት ወደ አንድ መቶ አስራ ምናምን ሺ የቡና ችግኞች እናደርሳለን ብለን አስበናል። እንዲህ ሲባል ሌሎች የጥላ ዛፎችና የሚበሉ ዛፎች እንደተጠበቁ ሆነው ማለት ነው። ለዚህ ዋቢ የሚባል ለብቻ የራሱ የሆነ ጣቢያ አለን። በዚህ ጣቢያ ብቻ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ችግኞች እናባዛለን።

**አዲስ ዘመን፡- ያጋጠማችሁ ችግሮች ካሉ ቢጠቅሷቸው? ይበልጥ ደግሞ ልትሰሩ ያቀዳችሁት ምንድን ነው?**

**ዮሐንስ (ዶ/ር)፡-** ሁሉም ተቋም ላይ ይበዛል ብዬ የማስበው የግዥ ሥርዓቱን ነው። እኛ ዘንድ ለተመራማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ የምንገዛቸው ኬሚካሎች እና ግብዓት የምንጠይቀው በተፈለገው ቁጥር ያህል አይደለም። ለጨረታ የሚሆን አይደለም። አንድ ተመራማሪ ትንሽ ያህል ሚሊ ነገር ነው የሚፈልገውና እሷን ለማግኘት አቅራቢ ማግኘት በጣም ከባድ ነው። የእኛ የግዥ ሥርዓታችን ችግር ባይሆንም ወደምርምሩ ሲመጣ ውስብስብ ይሆንብናል። በብዛት (ማስ) የሚገዛ አይደለም።

ለምሳሌ አንድ ተመራማሪ የሚፈልጋት ነገር በጣም ትንሽ ነች። እሱን ጨረታ ለማውጣት ከባድ ነው። ከዚህ የተነሳ አቅራቢዎችን ማግኘት በጣም ከባድ ነው። ስለዚህ ትንሽ የግዥ ሥርዓቱ ማነቆ ይሆንብናል።

ከዚህ ውጭ የበጀት እጥረቱ ውጭ ባሉ ደጋፊዎች ለማካካስ ነው ጥረት የምናደርገው እንጂ ከመንግሥት ብቻ የምንጠብቀው አይደለም። ምርምር ሲሰራ የግድ ከመንግሥት ትሬዠሪ ሳይሆን ከሌሎች ድጋፍ ከሚያደርጉ ድርጅቶችም ፕሮፖዛል በመጻፍና አጋርነት በመፍጠር ጥረት እናደርጋለን። ስለዚህም እየሰራን ያለነው በእዛ መልኩ ነው። እኔ እንደ ችግር ላነሳ የምችለው የግዥ ሥርዓቱን ነው። እንዳልኩት የግዥ ሥርዓቱ ለምርምር የሚመች አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- ዩኒቨርሲቲው ከሀገር ውስጥ ቀደምት ከሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች እና ከውጭ ሀገር ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?**

**ዮሐንስ (ዶ/ር)፡-** ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በተለይ ሀገር ውስጥ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ለምሳሌ ከእነ ጅማ ጋር የጅማ ክላስተር ነው፤ ከእነ አርባ ምንጭ ጋር በተለይ ከእንሰት ጋር ተያይዞ አብረን ለመሥራት የጋራ ስምምነት አድርገናል።

አዲስ አበባ እናት ዩኒቨርሲቲ እንደመሆኑ ሁሉንም የሚያግዝ ነው። ከሌሎች ማለትም ከደብረ ማርቆስ ጋርም ከእንሰት ጋር ተያይዞ ምንም እንኳ ገና ወደ ተግባር ባይቀይሩትም ወደእነርሱ አካባቢ ለማስፋፋት ትብብር አለን። ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከድርጅቶች፣ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከባዮ ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እና ከሌሎችም ጋር የምንሠራው አብረን ነው።

ከውጭ ደግሞ ከቻይና ዩኒቨርሲቲ ጋር ጆይንት የፒ ኤች ዲ ፕሮግራም በፊዚክስ አለን። ሕንድ ላይም አለን። እንዲሁ አውሮፓ እና አሜሪካም በቅርቡ የዩኒቨርሲቲያችን ፕሬዚዳንት ተፈራርመው መጥተዋል። በእስካሁኑ ሒደት ያለን ጥሩ የሚባል ግንኙነት ነው።

አዲስ ዩኒቨርሲቲ እንደመሆናችን መስፋፋት ያስፈልጋል። ስለዚህ ከፍ ያለው ቦታ ላይ እንገኛለን ማለት አይቻልም። አንዱ መሻሻል አለበት ብለን የምናስበው ኢንተርናሽናል ትብብርን ነው። ጥሩ ቢሆንም ብዙ መሻሻል ያለበት ነገር ግን አለ።

**አዲስ ዘመን።- ስለሰጠን ሰፊ ያስ ማብራሪያ እናመሰግናለን።**

**ዮሐንስ (ዶ/ር)፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የዳያስፖራው የኢንቨስትመንት ተሳትፎ - በኦሮሚያ ክልል

ወርቅነሽ ደምሰው

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ለሁሉም የኢንቨስትመንት መስኮች ሊውሉ የሚችሉ በርካታ የኢንቨስትመንት አማራጮች አሉት። በተፈጥሮ ሀብት የበለጸገ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪም በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርናው፣ በኢንዱስትሪና እና በአገልግሎት ዘርፎች ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ሰፊ አማራጮች አሉት። በርካታ ባለሀብቶችም እነዚህን የኢንቨስትመንት አማራጮች በመጠቀም ያላቸውን መዋዕለ ንዋይ ሥራ ላይ በማዋል በተለያዩ ኢንቨስትመንት ዘርፎች ተሰማርተው ኢንቨስትመንት እያደረጉ ይገኛሉ።

የክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ በክልሉ እስከ 2010ዓ.ም ድረስ ባሉት ዓመታት አንድ ሺ 23 ኢንቨስትመንቶች ብቻ የነበሩ፤ ባለፉት አምስት ዓመታት ዘርፉ ማሻሻል በማሳየቱ 13 ሺ 900 ኢንቨስትመንቶችን መቀበል ችሏል። በዘንድሮው በጀት ዓመት እስከ አሁን የተመዘገቡ ኢንቨስትመንቶች ከባለፉት ዓመታት ብልጫ አላቸው።

በክልሉ በተለያዩ ኢንቨስትመንት ዘርፎች ከተሰማሩት እና ለመሰማራት ከሚፈልጉ ኢንቨስተሮች መካከል ዳያስፖራዎች ይገኙበታል። በክልሉ በተለያዩ ኢንቨስትመንት ዘርፎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዳያስፖራዎች የተሰማሩ ሲሆን፣ በተለይ በ2014 እና በ2015 ዓ.ም ብቻ በተለያዩ ኢንቨስትመንት ዘርፎች (በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርናና በአገልግሎት ዘርፎች) 395 የሚሆኑ ዳያስፖራዎች ተሰማርተው ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል ፈጥረዋል።

የክልሉ መንግሥት ባለፈው ሳምንት በክልሉ ኢንቨስትመንት ላይ ለመሰማራት ከሚፈልጉ የዳያስፖራ አባላት ጋር ምክክር አድርጓል። ምክክሩ የኢንቨስትመንት መስኮችን ለማስፋት በሚያስችሉ ጉዳዮችና የኢንቨስትመንት ዘርፎችን እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችም ላይ አተኩሮ ነው የተካሄደው። በመድረኩም የዳያስፖራ አባላት፣ የክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊዎች እና የሚመለከታቸው አካላት ተገኝተዋል።

የክልሉ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ኤርሚያስ ደነቀ የኦሮሚያ ክልል ምቹ የኢንቨስትመንት አማራጮች እንዳሉት ጠቅሰዋል። ቀደም ሲል በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ሲሳተፍ የቆየው ዳያስፖራ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ ደግሞ በተለያዩ ኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ የመሳተፍ እድሉን አግኝቷል ይላሉ። ዳያስፖራው በበለጸጉት ሀገራት የሚኖር መሆኑን ጠቅሰው፣ በሚኖርበት ሀገር ያለውን እውቀትና ቴክኖሎጂ ወደ ሀገሩ ይዞ በመምጣት ኢንቨስት እያደረገ ይገኛል ይላሉ።

አንድ ባለሀብት ወደ ሀገሩ መጥቶ ኢንቨስት ሲያደርግ ብዙ ነገሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው ያሉት አቶ ኤርሚያስ፤ በመጀመሪያ የያዘውን ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ አውሎ ተጨማሪ ገቢ በማግኘት እና ሀገር በማሳደግ የራሱን ኃላፊነት መውጣት እንደሚፈልግ ይገልጻሉ። ከሁሉም በላይ ለሀገሩ ሲቆረቆር የነበረው ዳያስፖራ ለሀገሩ የሚያደርገው ነገር ያረካዋል፤ ያስደስተዋል፤ ለሀገሩ ያደረገው እንደ ውለታ ሳይሆን የራሱ ኃላፊነት እንደተወጣ ይሰማዋል ይላሉ።

«ዳያስፖራው ይህንን ሲያደርግ እንደ ሀገር እኛ የምንጠቀመው ይኖራል። ሀገር ገቢ ታገኛለች፤ ታድጋለች፤ ቴክኖሎጂ ይኖራታል፣ በሚፈጠረው የሥራ እድል ተጠቃሚ ትሆናለች። የሀገሪቱን የውጭ ግንኙነትም ይጠናከራል» ሲሉ ጠቅሰው፣ ለእዚህ ሁሉ ዳያስፖራው የሀገሪቱ አምባሳደር መሆን እንደሚጠበቅበት አስገንዝበዋል።

በክልሉ ቀደም ባሉት ጊዜያት የዳያስፖራው የኢንቨስትመንት ተሳትፎ ብዙ እንዳልነበረ አስታውሰዋል። እስከ 2012 ዓ.ም የነበረው የኢንቨስትመንት ተሳትፎ 403 መሆኑን ጠቅሰው፤ በ2014ዓ.ም፣ 150፤ በ2015ዓ.ም 239 እና በ2016 ባለፉት ወራት 73 ዳያስፖራዎች በክልሉ ኢንቨስትመንት ዘርፎች መሰማራታቸውን ገልጸዋል። የባለፉት ሶስት ዓመታት የዳያስፖራው የኢንቨስትመንት ተሳትፎ ከቀደሙት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር ብልጫ እንዳለው ያሳያል።

ቀደም ሲል በመንግሥትና በዳያስፖራው መካከል መራራቅ ነበር ያሉት አቶ ኤርሚያስ፤ አሁን ላይ ችግሮች ሙሉ ለሙሉ ተቀርፈዋል ማለት ባይቻልም ለውጦች ለመኖራቸው ብዙ ማሳያዎችን ማንሳት እንደሚቻልም ተናግረዋል። ዛሬ አላሠራ ያሉ እንቅፋቶችም ነገ እንደሚፈቱ እምነታቸው መሆኑን ተናግረዋል። «ትናንትና ያጋጠሟችሁን ፈተናዎች ያለፋችሁ ዳያስፖራዎች በቀጣይም ለችግሮቻችሁ ሳትንበረከኩ ከችግሮቻችሁም በላይ ሆናችሁ መፍትሔ እስኪታገኙ ድረስ መታገል ይጠበቅባችኋል» ሲሉ አስገንዝበዋል።



በምክክር መድረኩ የዳያስፖራ አባላት፣ የክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊዎች እና የሚመለከታቸው አካላት ተገኝተዋል፣

አቶ ኤርሚያስ እንዳሉት፤ እንደ ክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ ከዳያስፖራው ጋር በተለያዩ ጊዜያት ውይይቶች በማድረግ ባለሀብቱ (ዳያስፖራው) ያጋጠመውን ችግር ለመፍታት የሚያስችሉ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። ከእነዚህ ተግባራት መካከል አዋጅ 249/2015 እንዲወጣ ተደርጓል። የዚህ አዋጅ መውጣት በኢንቨስትመንት ዘርፉ ላይ ብዙ መሻሻሎችና ለውጦች እንዲኖሩ አስችሏል፤ ቀደም ሲል በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ጉዳያቸውን ለማስፈጸም በዞን ደረጃ 23 ቦታዎች ፤ በከተማ ደረጃ 11 ቦታዎች ላይ መድረስ ይጠበቅባቸው ነበር። አዋጁ ይህን መጉላላትና እንግልት በማስቀረት ጉዳያቸውን በሦስት እና በአንድ ቦታ ብቻ እንዲፈጽሙ አስችሏል።

የክልሉ መንግሥት ዳያስፖራው ሀገሩ መጥቶ ኢንቨስት እንዲያደርግ የሚያስችሉ ሥራዎችን ቀን ከሌሊት እየሠራ መሆኑን አቶ ኤርሚያስ ተናግረዋል። በመንግሥት ቁርጠኛ ውሳኔም ዞን ላይ የሚፈለገው ሳይት ፕላንም በቢሮ ደረጃ እንዲሆን መደረጉን ገልጸዋል። በካቢኔ ተወስኖ ወደታች የሚጻፈው ደብዳቤ ቀርቶ በክልል ደረጃ ዳያስፖራውም ሆነ ባለሀብቱ ከተስተናገደ በኋላ ወደ ዞን የሚሄደው ካርታ ለመውሰድ ብቻ እንዲሆን ተደርጎ አቅጣጫ ተቀምጦና ደንብ ወጥቶ እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል።

እነዚህ ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም ዳያስፖራው ትልልቅ ኢንቨስትመንቶች ላይ መሥራት ይጠበቅበታል ያሉት አቶ ኤርሚያስ፤ ዳያስፖራው ኢንቨስት ለማድረግ ወደ ሀገሩ ሲመጣ ኅብረተሰቡ የሚማርበት፤ ለትውልዱ በሚጠቅም ከፍ ያለ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ መሰማራት እንደሚኖርበትም ያመላክታሉ። ዳያስፖራ ብዙ ልምድ፣ እውቀት፣ ቴክኖሎጂና ሀብት ያለው መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህን የሚመጥን የኢንቨስትመንት ዓይነት ይዞ መምጣት አለበት ብለዋል።

ዳያስፖራው ይህን ሲያደርግ የክልሉ መንግሥት ድጋፍ ያደርጋል ያሉት ምክትል ኃላፊው፣ «ዳያስፖራ አንድ ፋብሪካ ይዞ ቢመጣ ፋብሪካው ሲገነባም ወደ ማምረት ሥራ ሲገባም ለመቶና ከዚያ በላይ ለሆኑ ዜጎች የሥራ እድል ይፈጥራል» ሲሉ የኢንቨስትመንቱን ፋይዳ አብነት ጠቅሰው አመልክተዋል።

አቶ ኤርሚያስ፤ ያደጉት ሀገራት የኢንቨስትመንት መስክ ተሞክሮ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ መሰማራት አዋጭ መሆኑን እንደሚጠቁም ጠቅሰው፣ የዳያስፖራው የኢንቨስትመንት ጥያቄ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ የተመሠረተ ቢሆን የተሻለ ነው ሲሉ ምክረ ሃሳብ ለግሰዋል።

እንደ ምክትል ኃላፊው ማብራሪያ፤ የክልሉ መንግሥት ለኢንቨስትመንት ዘርፉ እንቅፋት የሆኑ አዋጆችንና መመሪያዎችን አስወግዷል። የሸገር ከተማ የኢንቨስትመንት ጉዳይ በዚያው በሸገር እንዲስተናገድና ውሳኔ እንዲሰጥና ድጋፍ እንዲደረግ የሚያስችል አሠራር ተዘርግቷል። በአግሮ ፕሮሰሲንግ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ዳያስፖራዎችም ቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ክፍት የተደረገ ሲሆን፤ ዳያስፖራው በዚህ ፓርክ ኢንቨስት ማድረግ ይችላል። በሌሎች የኢንቨስትመንት መስኮችም የተቀናጀ ኢንቨስትመንት እንዲኖር ለማድረግ እየተሠራ ነው።

በምክክር መድረኩም የዲያስፖራ አባላትም በክልሉ ኢንቨስትመንት ላይ ለመሳተፍ ሲንቀሳቀሱ ያጋጠሟቸውን ችግሮች አንስተዋል። ከተነሱት ሃሳቦች መካከል በመድረኩ ተሳታፊ የሆኑት አንድ የዳያስፖራ አባል የሕፃናት ወተት የሚያመርት ፋብሪካ በሀገር ውስጥ መገንባት ፈልገው በተደጋጋሚ ቢመላለሱም ምላሽ የሚሰጣቸው አካል ጠፍቶ ወደ ሥራ መግባት እንዳልቻሉ ጠቅሰው፣ መንገዱ ዳገት ሆኖባቸው እንዳሰቡት ሳይሆን ወደኋላ እየተመለሱ እንደሆነ ተናግረዋል።

ሌላኛው ተሳታፊ በበኩላቸው በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለመሰማራት ፈልገው ሳይት ፕላን ከተሰጣቸው ሁለት ዓመት መሆኑን ተናግረው፤ እስካሁንም ምንም ምላሽ እንዳልተሰጣቸው አመልክተዋል። በግብርና ላይ ለመሰማራት ፈልገው እንቅስቃሴ ከጀመሩ ከዓመት በላይ እንደሆናቸው የተናገሩት እኚህ ባለሀብት፣ እስካሁን ድረስ ምንም ዓይነት ውሳኔ እንዳላገኙ ገልጸዋል።

መድረኩ ዳያስፖራዎች ጥያቄዎቻቸውን ያቀረቡበት ብቻ አልነበረም፤ አሁን እየታየ ያለውን ለውጥ ያደነቁበትም ነበር። ከለውጡ ወዲህ መንግሥት ዳያስፖራው ወደ ሀገሩ ገብቶ እንዲያለማ እያደረገ ያለበት ሁኔታ አድንቀዋል። አሠራሮች እየተሻሻሉ መምጣታቸውን ጠቅሰው፣ የበለጠ ለውጥ ማምጣት እንደሚገባም ጠቁመዋል።

«የዳያስፖራ አባላት ያነሷቸው ችግሮች በአጠቃላይ ካሉት ችግሮች አንጻር ሲታዩ በጣም ኢምንት ናቸው፤ ብዙዎቹ ችግሮች አልተነሱም» ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ ዳያስፖራው አሁን ላይ ያሉ ጅምር ሥራዎችና የመንግሥትን ቁርጠኝነት በመመልከት ብቻ ብዙ ጥያቄዎች አላነሳም ብለው እንደሚያምኑ ይናገራሉ። «በክልሉ ኢንቨስትመንት ላይ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ለውጦች ታይተዋል፤ በርካታ ሥራዎችም ይቀራሉ። ይህን አሠራር ለማሻሻል እየተወሰደ ያለው ርምጃ ተጠናክሮ ይቀጥላል» ሲሉ ተናግረዋል።

የቀድሞው አሠራር ጎታች እንደነበር አስታውሰው፣ ይህንን ለመለወጥ ጥረቶች መደረጋቸውን ተናግረዋል። በዚያ አሠራር ባለሀብቱ መሬት ማግኘት ላይ ችግር ይገጥመው እንደነበር ጠቅሰው፣ አሁን ፈቃድ ያገኘ ባለሀብት መሬት እስኪያገኝ ድረስ ከተማው ወይም ዞኑ መሬት ለሌላ ባለሀብት እንዳይሰጥ ተከልክሏል ይላሉ። «ይህ ማለት ለእናንተም ዘንድሮ ውሳኔ ከተሰጠ እናንተ መሬት ሳታገኙ ለሌላ ባለሀብት መሬት አይሰጥም» ማለት ነው ሲሉ ያስረዳሉ ።

ምክትል ኃላፊው፤ በኢንቨስትመንቱ ረገድ የሚነሱ መሻሻልና መስተካከል ባለባቸው ነገሮች ላይ መሥራትን እንደሚጠይቅም አስታውቀዋል። አንዳንድ የዳያስፖራ አባላትም ሊያስተካክሏቸው የሚገቡ ጉዳዮች እንዳሉም ጠቁመው፣ ባደጉት ሀገራት ያለውንና የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት እንደሚጠበቅባቸውም ተናግረዋል።

የሸገር ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ ኃይለሚካኤል ዓለሙ (ዶ/ር)፤ በበኩላቸው ከዳያስፖራው የተነሳው የመኖሪያ ቤት ጥያቄ በተለየ መልኩ የሸገር ከተማን እንደሚመለከት ጠቅሰው፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ብዙ ችግሮች የሸገር ከተማንም ይመለከታሉ ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ዳያስፖራው ያነሳቸው የሸገር ከተማን የሚመለከቱና መስተካከል ያለባቸውን ጉዳዮች ለማስተካከል ይሰራል ያሉት ኃይለሚካኤል (ዶ/ር)፣ የክልሉ መንግሥት የዳያስፖራው የመኖሪያ ቤት ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል የተለየ ፓኬጅ በሸገር ከተማ ለማዘጋጀት እየሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል። እንደ ሸገር ከተማ የተለያዩ ፓኬጆች ተዘጋጅተው፤ ዲዛይን ተዘጋጅቶላቸው፣ ቀሪ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውንም አስረድተዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፡ የሸገር ከተማ በጣም ሰፊና በሁሉም መስኮች ለኢንቨስትመንት ምቹና ሞዴል ከተማ ናት። በኢንቨስትመንቱ ረገድ ከተማዋ እያደረገች ያለችው ዝግጅት በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ትልቅ እድል ያለው ነው።

እስካሁን በከተማዋ የኢንቨስትመንት አገልግሎቶችን መስጠት አልተጀመረም ሲሉም ተናግረው፣ ምክንያቱም ከተማዋ በቅርብ የተመሠረተች እንደመሆኑ ስትራቴጂ በማዘጋጀት የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ለመሥራት ታስቦ እንደሆነ ገልጸዋል። አሁን ላይ በቂ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አመልክተው፣ ዝግጅቱ ሲጠናቀቅ የዘገየውን ያህል በእጥፍ ፍጥነት ለመጓዝ የሚያስችል ሥራ እንደሚሰራ ተናግረዋል። በተለይ በኢንቨስትመንት ረገድ የሚሰጠው አገልግሎት የተቀላጠፈ እንዲሆን ለማድረግ ይሠራል ሲሉ ገልጸዋል።

እስካሁን ከተማዋን የሚመጥን ስታንዳርድና የመለያ መስፈርት እየተዘጋጀ ነው ያሉት ኃላፊው፤ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ለማዘጋጀት፣ የቴክኖሎጂ አሠራሮች ተግባራዊ ማድረግ ላይ እየተሠራ መሆኑን ይናገራሉ። ዳያስፖራው ባለበት ቦታ ሆኖ በቴክኖሎጂ ተጠቅሞ በሀገሩ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ የሚያስችል አሠራር እንዲኖር እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ በጥቂት ጊዜያት ውስጥ አገልግሎት መስጠት እንደሚጀመርም አስታውቀዋል።

ከዚህ በተጨማሪም በሸገር ከተማ ኢንቨስትመንት ለመሰማራት ለሚፈልጉ አካላት የሸገር ከተማ አስተዳደር ያለምንም ወጣ ውረድ እዚያው ሸገር ከተማ ለማስተናገድ እንደሚሰራ ገልጸዋል። ሸገር ማስተር ፕላን ያላት ከተማ መሆኗን ገልጸው፣ «ሞዴል የሆነ ኢንቨስትመንት ይዞ የመጣ ዳያስፖራ በሚገባ ይስተናገዳል» ሲሉም ተናግረዋል።

# ጎሜ

# የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ያጋለጠው ሰሞነኛው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብልሽት

**አሲ ሴሮ**



ባለፈው ሳምንት ማብቂያ ዓርብ መጋቢት 6 ቀን 2016 ዓ.ም. ምሽት ላይ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የገንዘብ ዝውውር ሥርዓት ላይ ችግር ተፈጠረ። የተፈጠረው ችግርም ከባንኩ የዲጂታል ሥርዓት ጋር የተያያዘ መሆኑን የባንኩ የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል። በዚሁ ችግር ምክንያትም የባንኩ መደበኛ አገልግሎቶች ለተወሰኑ ሰዓታት መቋረጣቸው ይታወቃል።

በወቅቱም ከ490 ሺህ በላይ ጤነኛ እና ሕጋዊ ያልሆነ ግብይት መከናወኑን ፕሬዚዳንቱ ጠቅሰው በዚህ ሂደትም የተዘዋወረ ገንዘብ ወጪ እንዳይሆን መታገዱን አንስተዋል። በዚህ ሂደት ውስጥ የተከናወኑ ግብይቶችን የመመርመር ሥራው መቀጠሉንና በተለይም ከፍተኛ ግብይት ያከናወኑትን ለፀጥታ አካላት ማሳወቅ መቻሉንም ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በገንዘብ መክፈያ እና ማዘዋወሪያ ሥርዓቱ ላይ ያጋጠመው ችግር በተለይ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ዘንድ በስፋት ተሰራጭቷል። ከሌሊቱ 6 እስከ 8 ሰዓት ድረስ ተማሪዎች በብዛት ሲደዋወሉ እንደነበረ እና አንዳንዶቹም ‹‹ቢዝነስ እንሥራ በሚል›› ለሩቅ ዘመዶቻቸው ጭምር እየደወሉ ሲያሳውቁ ነበር። ከዛም አልፎ ሁሉም በዘረፋው እንዲሳተፍ በማኅበራዊ ሚዲያ ጭምር መልዕክት ሲተላለፍ ነበር።

በተጨማሪም በምሽት በትምህርት ተቋማቱ ውስጥ እና በአቅራቢያው ባሉ የገንዘብ መክፈያ ማሽኖች (ኤቲኤም) አካባቢ ረዣዥም ሰልፎችን ሠርተው ጥሬ ገንዘብ ወጪ ሲያደርጉ እንደነበረ ተማሪዎች ለቢቢሲ አማርኛ ዝግጅት ክፍል ተናግረዋል። እስካሁን ያልመለሱ ተማሪዎችም ገንዘቡን እንዲመልሱ ጠይቀዋል። ይህንንም ተከትሎ በባንክ ሂሳባቸው በቂ ገንዘብ ሳይኖራቸው በርከት ያለ የገንዘብ ዝውውር ፈጽመዋል የተባሉት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መሆናቸው ተሰምቷል። ፕሬዚዳንቱ አቶ አቤ እንደተናገሩት ተማሪዎቹ የእራሳቸው ባልሆነው የገንዘብ ዝውውር ውስጥ የገቡት ባንኩ የሳይበር ጥቃት አጋጥሞት እንደሆነ እና ሊደረስብን አይችልም በሚል የተሳሳተ ግምት ነው ብለዋል።

ይህን ጉዳይ አስመልክቶም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አቢ ሳኖ በዚህ ድርጊት ላይ የተሳተፉት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መሆናቸውን ገልጸዋል። ንግድ ባንክም የብዙዎቹን ተማሪዎች ስም ይፋ አድርጓል። ለመሆኑ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በዚህ አይነቱ ሕገ ወጥ ድርጊት እንዴት ሊሳተፉ ቻሉ? የሀገርና የሕዝብ ንብረት ሲዘረፍ ዋና ተዋናይ ሆነው የተገኙበት ገፊ ምክንያትስ ምንድን ነው? የሚሉና መሰል ጥያቄዎች በብዙዎች ዘንድ ሲመላለስ ሰንብቷል።

የተማሪዎቹን ሕገወጥ ድርጊት የትምህርት ሥርዓቱን ውድቀት ፍንትው አድርጎ ያሳየ ነው የሚሉ ብዙዎች ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ የዘለቀው የትምህርት ፖሊሲ ለሀገሪቱ የትምህርት ጥራት መውደቅ በዋነኛ ተጠያቂ ሆኖ ሲተች ቆይቷል። በተማሪዎች ብቃት እንዲሁም በአንዳንድ ቦታም በመምህራን የማስተማር አቅም ላይ ሳይቀር ያስከተለው አሉታዊ ተጽዕኖ ዛሬ በየደረጃው እየታየ መሆኑን በመረጃ የሚሞግቱ አሉ።

በሌላ በኩል የብሔራዊ ፈተና ስርቆቶች የአደባባይ ጉዳይ ከሆኑ የሰነበተ እንደመሆኑ ድርጊቱ ከማኅበረሰብ ሞራል ይዞታ ጋር ያያይዛሉ። በዚህ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የሚወጣው ተማሪ ምን ያህል ብቃት ያለው እና ኃላፊነት የሚሰማው በሥነምግባርም የታነጸ ነው የሚለውን አጠያያቂ አድርጎታል።

ጎበዝ ተማሪዎች እንዳሉ ሆነው አብዛኛው ተማሪ ግን በፈተና ስርቆት ጭምር የሚጠረጠር ነው። ስለዚህም ፈተና በመስረቅና በመኮረጅ የሚታማው ተማሪ ብር ሲያገኝ ወደ ዘረፋ መግባቱ የሚያስገርም አይደለም የሚሉ ብዙዎች ናቸው። ‹መማር ያስከብራል፤ አገርን ያኮራል› በሚል ለትምህርት ከፍተኛ ቦታ ለሚሰጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተማሪዎቹ ድርጊት አንገት የሚያስደፋ ነው።

አሁን ያሉት ተማሪዎች ያለፉት ሃያ ዓመታት የተበላሸ ሥርዓተ ትምህርት ውጤት ናቸው። ከእነዚህ መሐል ጥቂት የሚባሉ (በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና እንደታየውም ከ3 በመቶ ያልበለጡ) ችግሩን ተሻግረው ለሀገርና ለወገን የሚጠቅሙ ዜጎች የሚሆኑ ታይተዋል። ብዙኃኑ ግን አሁንም በቂ ክትልልና ድጋፍ የሚሻ ነው። አልፎ ተርፎም እንደሰሞኑ አይነት ሕገ ወጥ ድርጊት ሲታይ ወቀሳ ጭምር ከማኅበረሰቡ ሊሰማ ይገባል። የራሳቸው ያልሆነን ገንዘብ ከባንክ የሰረቁና ለመስረቅም የሚሞከሩ ተማሪዎች ሊወቀሱ ይገባል።

ይህ ሳይሆን ሲቀር ግን ዜጎች ለሀገር ሸክም ይሆናሉ። የተሠራን የሚያጠፉና የሚያወድም ትውልድም ይፈጠራል። ከወቀሳው ጎን ለጎን ግን ለዚህ ታዲያ ቁልፍ መሠረቱ የትምህርት ሥርዓቱ መሆኑን መተማመን ይገባል። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የፈጸሙት የገንዘብ ስርቆትም የየትምህርት ሥርዓቱ ምን ዓይነት ተማሪዎችን እያፈራ እንዳለ አመላካች ነው።

ዩኒቨርስቲዎች የዕውቀት ማዕከሎች፤ የክርክርና የውይይት መድረኮች ናቸው። ኢሞራላዊ ድርጊቶች የሚወገዙበት ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅሙ ሃሳቦች የሚንሸራሸሩባቸው ማማዎች ናቸው። አልፎ ተርፎም የሀገር ወደ ኋላ መቅረትና የሕዝብ ብሶትና ግፍ ይበቃል በሚል ሕይወታቸውን ጭምር የገበሩ ምሑራን የፈለቁባቸው አውድማዎች ናቸው። በተገኘው አጋጣሚም እውቀትን ከብዕርና ወረቀት ጋር በማገናኘት ኢ-ሞራላዊ ድርጊቶችን ሲያወግዙና ሲተቹ የቆዩ በርካታ ምሑራንን ያፈሩ የዕውቀት በሮች ናቸው።

የተማሩ ሰዎች በየትኛውም ጊዜና ቦታ የሰዎች ነፃነት ሲገፈፍና ፍትሕ ሲዛባ በይፋ በመናገርና በመፃፍ ተቃውሟቸውን ይገልፃሉ፤ ይሟገታሉ። ነፃነትና እኩልነት ሲረጋገጥም ድጋፍና ደስታቸውን በይፋ ይገልፃሉ። እነዚህ የነፃነትን ጣዕም የሚያውቁ በሁሉም ጊዜና ቦታ ለሰው ልጆች ነፃነትና እኩልነት ይሟገታሉ፤ ድንቁርናና ጭቆናን ፊት-ለፊት ይጋፈጣሉ፤ ለመላው የሰው ልጆች ነፃነትም መሟገት ይጀምራሉ።

በአጠቃላይ “ምሑራን” ወይም የተማረ ሰው ማለት ሃሳብና አስተያየታቸውን በአደባባይ በመግለፅ የሕዝብን ጥያቄ የሚያንፀባርቁ እንዲሁም ኋላ-ቀር አመለካከትና ግትር አቋምን በይፋ የሚሞግቱ አካላት ናቸው። በተጨማሪ የትምህርት ዋና ተግባር መሆን ያለበት አንድን ሰው እንዴት በትኩረት እና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ማሰብ እንዲችል ማድረግ እንደሆነ አጠቃላይ የትምህርት ሥርዓት ሂደት ያስረዳናል። አንድን ድርጊት ከመፈጸም በፊት ይህ ጉዳይ ጥሩ ነው ወይስ መጥፎ ፤ ሀገርን ይጎዳል ወይስ ይጠቅማል ብሎ በምክንያታዊነት ማሰብ የአንድ ምሑር የእውቀት መጀመሪያ ይመስለኛል።

ከራስ በፊት ለሀገርና ለወገን መቆርቆር፤ ለእውነት መቆም፤ በጅምላ ከማሰብ በፊት በግል ቆም ብሎ ማሰላሰልና ሞራላዊና ኢ-ሞራላዊ ድርጊቶችን መገንዘብ በትምህርቱ ዓለም ያለ ሁሉ የሚገነዘበውና የሚተገብረው ነው። ዛሬ ግን ይህ ሁኔታ እየኮሰመነ መጥቶ ይባስ ብሎም የሀገርና የሕዝብ ሃብትን በሌሊት መዘረፉን ሰምተናል። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ ‹‹ተማሪዎቹ የእራሳቸው ባልሆነው የገንዘብ ዝውውር ውስጥ የገቡት ባንኩ የሳይበር ጥቃት አጋጥሞት እንደሆነ እና ሊደረስብን አይችልም በሚል የተሳሳተ ግምት ነው›› በሚል የገለጹት ተማሪዎቹ ለሕሊናቸው ያላቸውን ታማኝነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባ ነው።

‹‹ሰው አየኝ አላየኝ፤ ተደረሰብኝ አልተደረሰብኝ›› ብሎ ኢሞራላዊ ድርጊት ማድረግ ከአንድ የዩኒቨርስቲ ተማሪ የሚጠበቅ አይደለም። ሆኖም ይህንን ድርጊት ሲያወግዙ የነበሩና በምንም አይነት መልኩ በዘረፋው ውስጥ ያልተሳተፉ በርካታ ተማሪዎች መኖራቸውንም ከግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚገባ ግን ልብ ሊባል ይገባል። የሆነ ሆኖ ግን በዚህ ድርጊት ውስጥ የተሳተፉ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ግን የብዙኃኑን ተማሪ ስም ማስነሳቱ አልቀረም።

በአጠቃላይ ግን ባለፉት አሥርት ዓመታት የትምህርት ሥርዓቱና ፖለሲው፣ ከመምህራን አሠለጣጠንና ስምሪት፣ ከነበረው የምዘና ሥርዓት፣ ከመዋዕለ ሕጻናት ጀምሮ ተማሪዎቹ ያለፉበት የትምህርት ሥርዓትና ሂደቱ በችግሮች የተሞላ መሆኑ በሥነምግባርም ሆነ በብቃት ተወዳዳሪ የሆኑ ምሑራንን ማፍራት እንዳይቻል አድርጓል። ሰሞኑን ከንግድ ባንክ ጋር የተያያዙ ችግሮችም ይሁኑ የፈተና ስርቆት የመሳሰሉ ኢ-ሞራላዊ ድርጊቶች የዛሬ ስብራት ሳይሆኑ ለዘመናት የቆዩና የከረሙ ችግሮች ናቸውና ዘለቄታዊ መፍትሔ የሚያሻው ነው።

የተማሪዎቹ ጥፋት እንዳለ ሆኖ ከዚህም አልፎ የትምህርት ሥርዓቱ ያስከተለው ጦስ መሆኑን አምኖ ከመቀበል ባሻገር የማኅበረሰቡን የሞራል እሴቶች መሸርሸርንም ያሳየ ክስተት ነው። አለመዋሸት፤ አለመስረቅ፤ ታላቅን ማክበር፤ ለታናሽ መታዘዝ፤ ሕዝብን መውደድ፤ ሀገርን ማፈቅር፤ የሰውን ገንዘብ አለመንካት፤ ወንድማማችነትና አንድነት የመሳሰሉት እሴቶች በሂደት እየተሸረሸሩ መምጣትና በምትካቸውም በአቋራጭ መበልጸግ፤ የራስ ያልሆነን መመኘት፤ መለያየት፤ መጠላትና መቆራቆዝ እና የመሳሰሉት ስፍራውን መቆጣጠራቸው እንደ ሀገር አዘቅት ውስጥ እየከተተን መሆኑን የሚያመላክቱ በርካታ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል።

> **የተማሪዎቹ ጥፋት እንዳለ ሆኖ ከዚህም አልፎ የትምህርት ሥርዓቱ ያስከተለው ጦስ መሆኑን አምኖ ከመቀበል ባሻገር የማኅበረሰቡን የሞራል እሴቶች መሸርሸርንም ያሳየ ክስተት ነው**

ከሁለት ዓመታት በፊት ዩኒቨርስቲዎች የትምህርትና የምርምር ተቋማት ከመሆን ይልቅ የተማሪዎች አሬሳ በገፍ የሚወጣባቸው የሁከትና የብጥብጥ ማዕከላት ሆነው እንደነበር የሚታወስ ነው። በወቅቱም ለብዙዎቻችን ጥያቄ ሆኖ የነበረው የዕውቀትና የምርምር ማዕከላት እንደሆኑና የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎች ማፍሪያ የሆኑት ተቋማት እንዴት በዚህ መልኩ ሰዎች ወደሚገዳደሉባቸው የጦር አውድማነት ሊቀየሩ ቻሉ የሚለው ነበር።

ብዕር መጨበጥ የሚገባው እጅ ስለትና የጦር መሣሪያ አንግቦ የወጣቶችን ነፍስ ሲነጥቅ መመልከት በእጅጉ ስሜት የሚነካ ነበር። ይህ እንግዲህ ሊሆን የቻለው ተማሪዎቹ ከየመጡበት አካባቢ በወረሱት የጥላቻ አስተሳሰብ የተነሳ እንደሚሆን መገመት አይከብድም። እንደማኅበረሰብ የገባንበት የጥላቻና የመለያየት ድባብ ተማሪዎቻችንንም መርዞ እርስ በእርሳቸው የሚገዳደሉ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። የሚገዳደሉ አካላትን መገሰጽና ወደ ትክክለኛው መስመር መምራት የሚገባቸው የትምህርቱ ተዋናዮች እራሳቸው የለየላቸው ነውጠኞች ሆነው ሲገኙ በወቅቱ ብዙዎቻችንን አስደንግጧል።

እንግዲህ ሰሞኑን በንግድ ባንክ ላይ የተፈጸመውም ኢ-ሞራላዊ ድርጊት ከዚሁ የሥነምግባር መውረድ እና እሴት መላላት ጋር የተያያዘ ነው። እንደማኅበረሰብ እሴቶች ሲላሉ የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎችም ከዚሁ የላላ ዕሴት ሊያመልጡ የሚችሉበት አጋጣሚ አይኖርም።

እንደ ሀገር እነዚህን የተዳከሙ እሴቶቻችንን ለመመለስ ጥረት ካላደረግን በሁሉም ዘርፍ የሚጠብቀን ውድቀት ነው። ሙስና፤ ብልሹ አሠራር፤ ተገልጋይ ማጉላላት፤ ማመናጨቅ፤ አርፍዶ መግባትና በሥራ ሰዓት ከቢሮ ውጭ መገኘትና የመሳሰሉት የእሴቶች መሸርሸር የፈጠረው ክፍተት ነው። በእነዚህ ጉድለቶች ውስጥ ያለፉ ተማሪዎችም የዕዳው ተሸካሚ መሆናቸው እሙን ቢሆንም ያሉበት ደረጃ ግን ይህንን ለማድረግ የሚፈቅድላቸው አይደለም።

የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ እንደሚባለው ነገ ተመርቀው የሥራ ዕድል የሚያገኙበትን ተቋም አብረው ሲያወድሙ ለተመለከተ ስለነገዋ ኢትዮጵያ መጨነቁ አይቀርም። ስለኢትዮጵያ የወደፊት ዕጣ ፋንታ ማሰቡ የግድ ነው።

ስለሆነም የተዳከሙትን ማኅበራዊ ዕሴቶቻችንን ማጠናከር የትምህርት ሥርዓቱን ማዘመንና ወጣቱ ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት አሁን እያጋጠሙ ካሉን ችግሮች ለማምለጥ ያስችለናል። በተለይም ደግሞ ትምህርት የሁሉም ነገር ቁልፍ እንደመሆኑ መጠን ጥራት ያለው ትምህርት ማዳረስ በክህሎትም ሆነ በሥነ ምግባር ብቁ የሆነ ዜጋን ለማፍራት ያስችላል።

# የዘመን ጥበብ

## ቤተ- መጻሕፍትን ለማህበረሰብ መገናኛ

አስናቀ ፀጋዬ




ከ 1 ነጥብ 4 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገባቸው 4 ሺ 600 የሚሆኑ መጻሕፍት በስጦታ ቀርበዋል፤

ድሮ ድሮ እንዲህ ቴክኖሎጂው እንደልብ ሳይስፋፋ በኢትዮጵያ አብዛኛዎቹ የሥነ ጽሑፍ ውጤቶች ለተደራሲያን የሚቀርቡት በጋዜጣ፣ በመጽሔትና በመጻሕፍት በኩል ነበር። ምን እንኳን ያኔ የነበረው የሕዝብ ቁጥር አነስተኛ ቢሆንም ከነዚህ የሥነ ጽሑፍ ውጤቶች ተቋዳሽ የነበረው ሰው ቁጥር ቀላል የሚባል አልነበረም። በተለይ ደግሞ ተማሪው፣ መምህሩ፣ አርቲስቱና ሌላውም ኅብረተሰብ ክፍል ጥሩ የማንበብ ባህል ነበረው።

ይሁንና አሁን አሁን አብዛኛው ሰው እጁ ላይ ባለው ተንቀሳቃሽ ስልክ የሚመጡ መረጃዎችን የማየትና የማንበብ አጋጣሚ ያለው ቢሆንም እንደ ከዚህ ቀደሙ ጥልቀት ያለው ንባብ የማድረግ ዝንባሌ የለውም። ረጃጅም ጽሑፎችንና ወፍራም ደርዝ ያላቸውን መጻሕፍት የማንበብ ፍላጎቱ ሞቷል። ከዚህ ይልቅ ቁንጽል ጽሑፎችን ብቻ ማንበብን ይመርጣል። በዚህም አሁን ያለው መጻሕፍትን የማንበብ ባህል በእጅጉ እየቀነሰ ስለመምጣቱ በድፍረት መናገር ይቻላል።

ለዚህም ይመስላል የኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ- መጻሕፍት አገልግሎት ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በተለያዩ መሪ ቃላት የንባብ ሳምንት ንቅናቄ በተለያዩ የክልል ከተሞች የጀመረው። በዚህ ዓመትም አገልግሎቱ ከሰሞኑ የንባብ ባህልን ለማሳደግ በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልል ዳውሮ ዞን ተርጫ ከተማ ‹‹ንባብ ለሁለንተናዊ ስኬት›› በሚል መሪ ቃል የንባብ ሳምንት መርሃ ግብር አካሂዷል።

በኢትዮጵያ ቤተ- መዛግብትና ቤተ- መጻሕፍት አገልግሎት የአብያተ መዛግብት አገልግሎት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ያሬድ ተፈራ እንደሚናገሩት፣ በመርሃ ግብሩ አስራ አምስት ትምህርት ቤቶች፣ መምህራን፣ ተማሪዎችና በአካባቢው ላይ ያሉ በንባብ ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማት ተሳትፈዋል። ተማሪዎች የንባብ ባህልን እንዲሳድጉ ለማስቻል ከአዲስ አበባ የመጡና የክልሉ ተወላጅ የሆኑ ደራሲያንና ገጣሚያን ተሞክሯቸውን እንዲያቀርቡ ተደርጓል።

በመርሃ ግብሩ ለአስራ አምስት ትምህርት ቤቶች፣ ለአንድ የሕዝብ ቤተ መጻሕፍትና ለአንድ ማረሚያ ቤት የሚያገለግሉ ከ 1 ነጥብ 4 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገባቸው 4 ሺ 600 የሚሆኑ መጻሕፍት በስጦታ ቀርበዋል። በተርጫ ከተማ በሚገኘው ማረሚያ ቤት ውስጥ ለሚገኙ ከ 1 ሺ 200 ለሚሆኑ ታራሚዎችና በማረሚያ ቤቱ ውስጥ ለሚገኝ ትምህርት ቤት በተመሳሳይ የመጽሐፍ ስጦታ ተበርክቷል። ታራሚዎችም የዚሁ መርሃ ግብር አካል ሆነው ሥነ- ጽሑፍ አቅርበዋል። ይህም ታራሚዎች በማረሚያ ቤት በሚቆዩበት ጊዜ አንብበው ራሳቸውን እንዲቀይሩና ወደ ማህበረሰቡም ሲቀላቀሉ ብዙ ነገር እንዳያመልጣቸው ያስችላል።

መሪ ሥራ አስፈፃሚው እንደሚያስታውሱት ተቋሙ የንባብ ባህልን የማሳደግ ሥራ የጀመረው ከ2006 ዓ.ም ወዲህ ነው። ከ2011 ዓ.ም በኋላም በተጠናከረ መልኩ ሥራውን አስቀጥሏል። በአብዛኛው በኢትዮጵያ ያሉ ትልልቅ ከተሞች እንዲሁም የወረዳ ከተሞች ላይ ተቋሙ እየሠራ ይገኛል።

ከትግራይ ክልል መቀሌ ጀምሮ ጎንደር፣ ደብረ ታቦር፣ ደብረ ማርቆስ፣ ባህርዳር፣ ሰመራ፣ አሶሳ እንዲሁም በቅርብ ዓመታት ደግሞ በዲላ፣ ሀዋሳ፣ ደብረ ብርሃንና በሌሎችም ክልሎች የንባብ ባህልን ለማሳደግ ሰፋፊ ሥራዎች ተሰርተዋል። በወረዳዎች በተለይ ተመሳሳይ ሥራ ተሰርቷል። ልዩ ቤተ መጻሕፍትን በአዲስ መልክ የማደራጀት ሥራም ተከናውኗል። በቀጣይም በባህር ዳር፣ ኮንሶ የሚገኙ ሌሎች ቤተ መጻሕፍትን በአዲስ መልክ ለማደራጀት እቅድ ተይዟል።

አገልግሎቱ በብዛት የሚሰራው ከትምህርት ቤቶች፣ ከማረሚያ ቤቶችና ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ነው። መጻሕፍት የሚሰጣቸው ተቋማት በአደረጃጀት ውስጥ ያሉ ናቸው። ስለዚህ ቀድሞ የሚደረገው ትምህርት ቤቶች፣ ማረሚያ ቤቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎችና የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ምን እንደሚፈልጉ፣ ምን ያህል ሰዎች እንዳሉና በየትኛው ደረጃ እንደሆነ ጥናት ይደረጋል። ይህንን መነሻ በማድረግ ለእነርሱ የሚጠቅም በአብዛኛው የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያግዝና የጠቅላላ እውቀታቸውን የሚሳድግ መጻሕፍት ተገዝቶ እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

በኋላ ላይ ደግሞ ተቋሙ መጻሕፍቶቹ በአግባቡ ጥቅም ላይ እየዋሉ ስለመሆናቸው ተመልሶ የሚያይበት መንገድ አለ። ከየክፍሉ የተዋቀረ የባለሙያዎች ቡድን ወጥተው ከዚህ በፊት የተሠሩ ሥራዎችን በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ያያሉ። ችግሮች ካሉ በመለየት እንዴት መስተካከል እንዳለባቸው መፍትሔ ይፈልጋሉ። ይህም ሥራ የቁጥጥርና በቀጣይ ለመሥራት የታሰበውን ሥራ ለማየትና ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚያስችል ነው።

መሪ ሥራ አስፈፃሚው እንደሚገልፁት፣ የንባብ ባህልን ለማዳበር ሰፊና ብዙ ሥራዎችን መሥራት ይጠይቃል። የበርካታ ተቋማትን ቅንጅትም ያስፈልገዋል። ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት አገልግሎት ከባህል፣ ስፖርትና ቱሪዝም ቢሮዎችና ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር እየሠራ ይገኛል። በሌላ በኩል ደግሞ ተቋሙ በተለያዩ ክልሎች ተዘዋውሮ በሚሰራቸው ሥራዎች ትምህርት ቤቶች፣ ማረሚያ ቤቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎችና የሕዝብ ቤተ-መጻሕፍት ሥራውን የራሳቸው አድርገው እንዲያስቀጥሉ የማድረግ ሥራም ይሠራል።

ለምሳሌ ደብረ ታቦርና መቀሌ ይህን የንባብ ሳምንት ሃሳብ በመውሰድ በየዓመቱ ማከናወን ጀምረው ነበር። የዚህ ንባብ ሳምንት ሁሌም በየዓመቱ መካሄድ ትልቁ ፋይዳ የሚሆነውም ሃሳቡን ተረድተው እንዲተገብሩት ነው። በዛውም ለቤተ መጻሕፍት ያላቸው እውቀትና አያያዝ እንዲጎለበት ነው። መጽሐፍ ሻጮች የሚሳተፉበት የመጽሐፍ አውደ ርዕይም አለ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የፓናል ውይይቶች ይካሄዳሉ። እነዚህ የፓናል ውይይቶች በቤተ መጻሕፍት፣ በቤተ መዛግብት፣ በዲጂታል ላይብረሪ ያሉትን ሁሉ በተቋሙ በኩል የሚሰሩ ሥራዎችና የሌሎችም ተቋማት ተሞክሮ ይቀርባሉ።

በጥቅሉ ፋይዳው ሲታይ ደግሞ በሀገሪቱ የንባብ ባህል እንዲጎለብት ማድረግ ነው። የንባብ ባህልን ለማሳደግ ደግሞ ቤተ መጻሕፍት በሚገባ መደራጀት ይኖርባቸዋል። በተለይ ደግሞ ማህበረሰቡ ቤተ- መጻሕፍትን የራሱ እንዲያደርገው፣ የውይይትና ንግግር ቦታ እንዲሆን ማድረግና ማነቃቃት ነው የተቋሙ ዋነኛ ፍላጎት። ይህንን ሥራ ደግሞ ደራሲያን በሶስትና አራት ወራት ውስጥ ማከናወን ይችላሉ።

በሌላው ዓለም ያሉ ቤተ መጻሕፍት የፀጥታው ንባብ እንዳለ ሆኖ የማኅበረሰብ የመሰባሰቢያ ቦታ እየሆኑ መጥተዋል። ለምሳሌ እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ደራሲዎች በቤተ መጻሕፍት ውስጥ ባሉ ካፍቴሪያዎች ስለሚበሉትና ስለሚጠጡት ሳይጨነቁ እየተዝናኑ ከወጣቶች ጋር እንዲገናኙ እድል ይፈጥርላቸዋል። እነርሱ ቤተ መጻሕፍትን የማኅበረሰቡ መገናኛ ማእከል አድርገዋቸዋል። ቤተ መጻሕፍት የመረጃ፣ የመዝናኛ፣ የእውቀትና የሥራ ቦታ ሆነዋል። ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ

**‹‹ቤተ መጻሕፍት የመረጃ፣ የመዝናኛ፣ የእውቀትና የሥራ ቦታ ሆነዋል። ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ግቢ ውስጥም እየታየ ነው። ይህን ማሳደግ ይገባል። ያኔ ቤተ መጻሕፍት የመገናኛ ቦታ ይሆናል። ››**

ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ግቢ ውስጥም እየታየ ነው። ይህን ማሳደግ ይገባል። ያኔ ቤተ መጻሕፍት የመገናኛ ቦታ ይሆናል።

መሪ ሥራ አስፈፃሚው እንደሚያብራሩት ባጠቃላይ የቤተ መጻሕፍት ጉዳይ በሀገር ደረጃ ትልቅ ትኩረት አግኝቶ እየተሠራበት አይደለም። እንዲያውም ‹‹አብርሆት›› የተሰኘው ቤተ መጻሕፍት በአዲስ አበባ ከተከፈተ ወዲህ ነው ቤተ መጻሕፍት በዚህ ደረጃ መታነፅ ይችላል ወይ? የሚለውን ያሳየውና ተነሳሽነትን የፈጠረው እንጂ ከዛ በፊት በነበረው ሁኔታ የንባብ ባህል በኢትዮጵያ በእጅጉ ቀንሶ ቆይቷል። ስለዚህ በበርካታ አካባቢዎች ላይ ቤተ መጻሕፍቶችን በአግባቡ ማነፅ ላይ ክፍተት ይታያል።

በሌላ በኩል ደግሞ በቤተ መጻሕፍት ሙያ ዩኒቨርሲቲዎች በትክክለኛው ደረጃ ምሁራንን እያፈሩ አይደሉም። ይህም የንባብ ባህልን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት እያጋጠሙ ካሉ ችግሮች ውስጥ አንዱ ነው። ምክንያቱም ቤተ መጻሕፍት ሲገነቡ ትክክለኛ ባለሙያዎች በቦታው መመደብ ስላለባቸው ነው። በቤተ መጻሕፍት ሙያ ውስጥ ያሉ ባለሙያዎች በደንብ መጠቀም እንዲችሉ መደረግ ያለበት ሥራም አለ።

ስለዚህ እነዚህ የንባብ ባህልን ለማሳደግ ማነቆ ከሆኑ ምክንያቶች ውስጥ በዋናነት ይጠቀሳሉ። ማነቆዎቹን መፍታት የሚቻል ከሆነ ግን የሚፈለገውን የንባብ ባህል በማዳበር የዜጎችን እውቀት መጨመርና አመለካከታቸውን ማሳደግ ይቻላል። ለዚህ ደግሞ ራሱን የቻለ ፖለሲ መቀረጽ ይኖርበታል። በተለይ ቤተ መጻሕፍት በሀገር አቀፍ ደረጃ በስፋት እንዲሰራበት የሚያስችል ፖሊሲ ያስፈልጋል። ዩኒቨርሲቲዎችም በቤተ መጻሕፍት የትምህርት ዘርፍ በሁሉም ደረጃ ማፍራት ይጠበቅባቸዋል። በዚህ የሙያ ዘርፍ ያሉ ሙያተኞችም ከሙያቸው ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች በልዩ ልዩ መልኩ መመቻቸት ይኖርባቸዋል።

የቤተ- መጻሕፍት ባለሙያዎችን ከማፍራት አኳያ ዩኒቨርሲቲዎች ትልቅ ድርሻ ያላቸው ቢሆንም የኢትዮጵያ ቤተ- መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት በቤተ መጻሕፍት ደረጃ የአንድ ወር የሥራ ላይ ሥልጠና ዓመቱን ሙሉ ይሰጣል። ሥልጠናው በሁለት መልኩ የሚሰጥ ሲሆን አንደኛው ከየክልሉ ለሚመጡ ሲሆን ሁለተኛው በዛ ያሉ ሰልጣኞች ካሉ እዛው ክልሉ ድረስ በመሄድ የሚሰጥ ሥልጠና ነው።

ይህም በአብዛኛዎቹ ዩኒቨርሲቲዎችና የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ተዳርሷል። ሥልጠናው ሰልጣኞች መሠረታዊ የቤተ መጻሕፍት እውቀት ኖሯቸው መጻሕፍት እንዲያሰባስቡና ቤተ መጻሕፍት እንዲያደራጁ ያስችላቸዋል። ሆኖም ከዚህ ላቅ ያሉ ሥልጠናዎችን መስጠት ይፈልጋል። ይህም ከዲፕሎማ እስከ ፒ ኤች ዲ ደረጃ ከፍ እያለ ሲሄድ የቤተ መጻሕፍት ባለሙያዎችን ቁጥር ያሳድገዋል።

ዲጂታል ቴክኖሎጂውም ቢሆን የንባብ ባህል እንዲቀንስ በማድረግ ረገድ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ቢኖረውም ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ሲታይ በኢትዮጵያ የዲጂታል ነገር ብዙ የተስፋፋ አይደለም። ነገር ግን ዲጂታል ቴክኖሎጂውን እንደ እድል መጠቀም ይቻላል። የኤሌክትሮኒክ ቤተ መጻሕፍቶችን በመገንባት ለተጠቃሚው ማቅረብ ይቻላል። ከዚህ ውጭ ግን ጥልቀት ያለው የንባብ ባህል እንዲመጣና ቁንፅል የሆነው የፌስ ቡክና የሌሎችም ማህበራዊ ሚዲያዎች ጽሑፎች ብቻ እንዳይነበቡ ትልቁና በዋናነት መሠራት ያለበት እውቀት ያላቸውን ሰዎች ከወጣቱና ከሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች አንባቢያን ጋር ማገናኘት ነው።

ደራሲዎች ስለህትመት ሳይጨነቁ እንዲፅፉ ማበረታታትና መሸለም ያስፈልጋል። ንባብ ሊያድግ የሚችለው ከቤተሰብ ጀምሮ ወደ ትምህርት ቤትና ወደ ማህበረሰብ እያለ ነው። ስለዚህ በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤትና በማህበረሰብና በተቋም ደረጃ ትልቅ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። እነዚህን ሁሉ ማድረግ ሲቻል ነው የንባብ ባህልን በኢትዮጵያ ማሳደግ የሚቻለው።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## እጅ ያልሰጡ ብርቱዎች

እዮሩስ ተስፋዬ

የአምስት ዓመቷ ልጅ ከእኩዮቿ ጋር እየተጫወተች ነበር። በጨዋታ መሀል አንድ ሕጻን ድንጋይ ወርውሮ መታት። ድንጋዩ ለዓይኗ ተርፎ ነበርና ዓይኗን ታመመች። ከዛሬ ነገር ‹‹ይሻላታል›› ተብሎ ቢጠበቅም ከሕመሟ ልትድን አልቻለም።

ሕመሟ እየባሰ ሲመጣ የተሻለ ሕክምና ፍለጋ ከጎንደር ወደ አዲስ አበባ መጣች። በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ህክምናዋን መከተታል ጀመረች። ከህክምናው በኋላ ትንሽ ትንሽ ማየት ጀምራ ነበር። ነገር ግን ብዙም ሊቀጥል አልቻለም። የያኔዋ ሕጻን የአሁኗ ወይዘሮ አዳነች ተካው የዚህ ታሪክ ባለቤት ናቸው።

ወይዘሮ አዳነች አንድ አይናቸው ሙሉ በሙሉ ማየት አቁሟል። አንዱም ቢሆን በጭላንጭል ነው የሚያየው። ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ የሰው ወይም የዓይነ ሥውራን በትር ይሻሉ።

የአንድ ልጅ እናት የሆኑት ወይዘሮ አዳነች በየዕለቱ የሚገጥማቸውን ነገር ወደ ጎን በመተው ራሳቸውን ለመቻል ጥረት ያደርጋሉ። በፍጹም የሰው እጅን ማየት አይመኙም። ‹‹ብራይት ወርልድ ፎር ብላይንድ ውሜን አሶሴሽን›› በተባለ በጎ አድራጎት ድርጅት አማካኝነት የእጅ ሥራ ስልጠናዎችን ከአንድም ሁለት ጊዜ ወስደዋል። ብሬል ተምረው ማንበብም ችለዋል። ድርጅቱ ለዳንቴል እና መሰል የእጅ ሥራዎች የሚሆን የክር ድጋፍ ሲያገኙ የተለያዩ የዳንቴል ሥራ ውጤቶችን በመሥራት እና በመሸጥ በሚያገኙት ገንዘብ ሕይወታቸውን ይመራሉ። ይህም አጥጋቢ አይደለምና ተጨማሪ ጧፍ እና እጣን በመሸጥ ኑሯቸውን ይገፋሉ።

ወይዘሮ አዳነች ስልጠና ከመውሰዳቸው በፊት ‹‹ሊከብደኝ ይችላል ቢሆንም እወጣዋለሁ›› የሚል ተስፋ እና ስጋት ነበራቸው። የዳንቴል ሥራዎችን መሥራት እንደሚችሉ ከማመን ባላፈ በወሰዱት ስልጠና ዛሬ ላይ ብዙ ዲዛይኖችን ለመሥራት በቅተዋል። እንደ ሹራብ፣ ስካርፍ፣ ኮፍያ እና ሌሎችንም ጥንቅቅ አድርገው ይሠራሉ። ደጋግመው እንደሚያነሱት እርሳቸውም ይሁን እንደርሳቸው ያሉት ዓይነ ሥውራን ሴቶች ግን የሠሩት የዳንቴ ሥራ ውጤቶች ተሰርቶ ይቀመጣሉ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ



**ብርቱዎቹ እንስቶች ለአካል ጉዳተኞች የተመቻቸ ነገር ቢኖር ችግሮችን ማቅለል እንደሚቻል ያምናሉ፣**

ገበያው እና ገበያተኛው የሚገናኙበት ዕድል ጠባብ በመሆኑ ነው። ይህ ዕድል ቢኖር ግን ወይዘሮ አዳነች ራሳቸውንም ሆነ አንዱ ልጃቸውን ያለምንም ስጋት ማስተዳደር ይችላሉ።

እንደ ምንጣፍ እና ስጋጃ ያሉ ምርቶችን ለመሥራት አቅሙም ፍላጎቱም እንዳላቸው የሚናገሩት ወይዘሮ አዳነች፤ የግብአት እንዲሁም የቦታ እጥረቱ የፍላጎታቸውን ያህል እንዲሠሩ አልፈቀደላቸውም። ስለዚህም መንግሥት የገበያ ትስስር በመፍጠር እና የመሥሪያ ግብአቶችን ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ጠይቀዋል።

ብዙ አካል ጉዳተኞች እጃቸውን ለልምና ሲዘረጉ ይስተዋላል። ለዚህም የተመቻቸ ነገር አለመኖር በምክንያትነት ይጠቀሳል። ይህንን በተመለከተ ወይዘሮ አዳነች ሲናገሩ፣ አካል ጉዳተኞች ወደ ልመና እንዳይገቡ እንዲሁም የገቡትንም ከልመና ለማውጣት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል። አካል ጉዳተኞች ሠርቶ መብላት ብቻ ሳይሆን ሕይወታቸውን በሚገባ መምራት እንደሚችሉ ብዙዎች በተግባር አሳይተዋል ይላሉ ።

ሌላው ከአካል ጉዳተኞች ጋር ተያይዞ ከሚነሱ ችግሮች መካከል የማሕበረሰቡ አመለካከት በዋነኝነት ይጠቀሳል። ጧፍ እና እጣን ሲሸጡ የሚያበረታታቸው እንዳለ ሁሉ ማየት አይችሉም ብሎ የሚያጭበረብሩ ሰዎች መኖራቸውን የሚናገሩት ወይዘሮ አዳነች፣ ባለማየታቸው ምክንያት እቃ ሲጥሉ የማይገባ ስድቦችን ተሰድበው እንደሚያውቁ ያስታውሳሉ። የዚህ ሁሉ ችግር የግንዛቤ እጥረት ነው። ሕብረተሰቡ ዓይነ ሥውራን ላይም ሆነ ሌሎች አካል ጉዳተኞች ላይ ያለውን አመለካከት እንዲያስተካከል ብዙ መሥራት እንደሚገባ ይናገራሉ።

በመሠረተ ልማት ችግር፣ በጦርነት፣ በኑሮ ውድነት እና በሌሎች ምክንያቶች የአካል ጉዳተኛው ሕይወት ፈታኝ እየሆነ መምጣቱን የሚናገሩት ወይዘሮ አዳነች፤ በመንግሥት በኩል ለአካል ጉዳተኛው የተመቻቸ ነገር መሥራት ቢቻል ችግሮችን ማቅለል እንደሚቻል ያምናሉ።

ስንዱ ስለሺ ከፊል የእይታ ችግር ያለባት ሴት ነች። ከ15 ዓመት በፊት ሁለቱም ዓይኖቿ ማየት ይችሉ ነበር። በገጠማት የነርቭ ሕመም ግን እይታዋ ተስተጓጎለ። ነገሮችን ወደ ዓይኗ ካላቀረበች በቀር ማየት አትችልም። ዛሬ ራሷን ለማብቃት ብዙ ጥረቶችን ታደርጋለች። የኮምፒውተር እና የብሬል ስልጠናዎችን ወስዳለች። በተጨማሪም እንደ ወይዘሮ አዳነች በ‹‹ብራይት ወርልድ ፎር ብላይንድ ዉሜን አሶሴሽን›› የበጎ አድራጎት ድርጅት አማካኝነት ባገኘችው የጥልፍ (የዳንቴል) ሥራ ስልጠና ወስዳ ለሶፋ፣ ለረከቦት፣ ለመሶብ፣ ፤ኮፍያ እና ለአንገት የሚሆኑ ስካርፎችን በመሥራት ላይ ትገኛለች። የሠራቻቸው ምርቶች ሲሸጡ ደግሞ የድርሻዋን ክፍያ ታገኛለች።

መጀመሪያ የእጅ ሥራ ለመሰልጠን ፍርሃት እንዳደረባት ያልሸሸገችው ስንዱ፣ በመማሯ እና በመሰልጠኗ የሙያ ባለቤት ከመሆን በተጨማሪ ብዙ ሰዎችን እንዳገኘችበት እና ብዙ እውቀት እንድትገበይ እንዳገዛት ትናገራለች። አካል ጉዳተኞችም ያገኙትን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም መማር እንዲሁም መሰልጠን ቢችሉ የሙያ ባለቤት ከመሆን ባሻገር ሌሎችን እስከማስተማር እንደሚችሉ ትመክራለች።

የማየት እክል ላለበት ሰው ከባዱ ሥራ የሚመስለው እንደ ዳንቴል ያለ የእጅ ሥራዎችን መሥራት ነበር። እርሷ ግን ይህንን ማድረግ ችላለች። ይሁን እንጂ የሠራቻቸው ኮፍያም ሆነ ሌሎች ምርቶችን ለመሸጥ ድርጅቱ ከሌሎች የሚሰጡት የባዛር ተሳትፎ ወይም ሌሎች ዕድሎችን ለመጠበቅ ትገደዳለች። መንግሥት የገበያ ትስስሮችም ሆነ ሌሎች አማራጮችን ካዘጋጀላቸው ግን የበለጠ ለመሥራት ፍላጎቱ እንዳላት ታስረዳለች። እርሷም ሆነች ሌሎች አካል ጉዳተኞች ምቹ ሁኔታዎች ከተመቻቸላቸው መሥራት እንደሚችሉ ምስክር መሆን እንደሚቻልም ገልፃለች።

በአጠቃላይ መንግሥት ዓይነ ሥውራንንም ሆነ ሌሎች አካል ጉዳተኞችን ለመደገፍ የሚሠሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ቢደግፍ፣ የመሥሪያ ቦታዎችን ቢያመቻችላቸው እና የገበያ ትስስር ቢፈጥርላቸው ከዚህ የበለጠ መሥራት እንደሚቻል ትገልፃለች።

# ዓለም አቀፍ

## ሜክሲኮ ከቴክሳስ ተይዘው የሚላኩ ስደተኞችን ፈጽሞ አልቀበልም አለች

ሜክሲኮ፣ የአሜሪካዋ ግዛት ባጸደቀችው ጠንካራ የስደተኛ ሕግ ምክንያት ከቴክሳስ ተይዘው የሚመለሱ ስደተኞችን አልቀበልም አለች።

የአገሪቱ መንግሥት “ሜክሲኮ ከቴክሳስ የሚመለሱ ማንኛውንም ስደተኞች በምንም ሁኔታ አትቀበልም” ብሏል። ሜክሲኮ ይህንን መግለጫ ያወጣችው የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሕጉ ተግባራዊ እንዲሆን መፍቀዱን ተከትሎ ነው።

ይህ ሕግ የቴክሳስ ፖሊስ የአሜሪካ - ሜክሲኮን ድንበር በሕገ ወጥ መንገድ አቋርጧል ተብሎ የተጠረጠረን ስደተኛ እንዲያስር ይፈቅዳል።

የባይደን አስተዳደር ኤስቢ4 የተባለውን ሕግ “ሕገ መንግሥታዊ ያልሆነ” ሲሉ ተቃውመውታል። ቀደም ብሎ ፍርድ ቤቶች የአገሪቷን የኢምግሬሽን ሕግ ማስፈፀም የሚችሉት ግዛቶች ሳይሆኑ የፌዴራል መንግሥቱ ብቻ ነው ብለው ነበር።

የአሜሪካን ድንበር በሕገ ወጥ መንገድ ማቋረጥ ወንጀል ቢሆንም እነዚህ ጥሰቶች የሲቪል ጉዳይ ተደርገው የሚታዩት በኢሚግሬሽን የፍርድ ቤት ሥርዓት ነው።

ኤስቢ4 ሕግ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ቴክሳስ የሚገቡ ስደተኞች እስከ 20 ዓመት የሚደርስ እስራት እንዲቀጡ ያዛል።

የሜክሲኮ ባለሥልጣናት ቀደም ብሎ ሕጉን ‘ፀረ ስደተኛ’ ሲሉ ሕጉን የተቹት ሲሆን፤ ከአሜሪካ ጋር ያለውን ግንኙነት ሊያወሳስበው እንደሚችልም አስጠንቅቀዋል። ይህ ስጋት በአሜሪካ የፍትሕ መሥሪያ ቤትም ተስተጋብቷል።

የሜክሲኮ የፍትሕ ሚኒስቴር ማክሰኞ ዕለት ባወጣው መግለጫ እንዳለው፤ ሜክሲኮ ግዛቶች አሊያም የአካባቢ ባለሥልጣናት ስደተኞችን እንዲቆጣጠሩ፣ ዜጎችና የውጭ ዜጎችን ማሰር እና መመለስ የሚፈቅደውን ሕግ አትቀበለውም።

መግለጫው ጨምሮም ሕጉ በቴክሳስ የሚኖሩ ወደ 10 ሚሊዮን የሚጠጉ ሜክሲኮውያን ሰብዓዊ መብት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል ብሏል።

የሜክሲኮ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም ኤስቢ4 ስደተኛ ማኅበረሰቦች ለጥላቻ ንግግርና ለአድልዎ በማጋለጥ አስከፊ ሁኔታን ይፈጥራል ብሏል።

ሚኒስቴሩ ኤስቢ4 ሕግን ለማስቆም በአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን የሚደረገውን ሕጋዊ ጥረት እንደሚቀላቀልም አስታውቋል።

ዋይት ሃውስ የፌዴራል የታችኛው ፍርድ ቤቱ ስለ ሕጉ ሕጋዊነት ላይ ጥያቄ ባነሳበት ሁኔታ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን ማስተላለፉን ተችቷል።

የዋይት ሃውስ ፕሬስ ሴክሬታሪ ካሪን ጂን ፔሪ በሰጡት መግለጫ “ኤስቢ4 በቴክሳስ ያሉ ማኅበረሰቦችን ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥል ብቻ ሳይሆን በሕግ አፈጻጸም ላይ ጫና ይፈጥራል። እንዲሁም በደቡባዊ ድንበር ላይ ትርምስ እና ግርታን ይፈጥራል” ብለዋል።

ሆኖም ሪፐብሊካኑ የቴክሳስ ገዥ ግሬግ አቦት፣ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ አዎንታዊ ለውጥ በማለት አወድሰውታል።

ምክትላቸው ዳን ፓትሪክም “ ሕገ ወጥ ስደተኞችን ማሰር እና ወደ ሜክሲኮ ጠርዞ መላክ አሊያም ወደ እስር ቤት መወርወር እንጀምራለን” ሲሉ ማክሰኞ ዕለት ለፎክስ ኒውስ ተናግረዋል።

ኤስቢ4 ሕግ የተፈረመው ታኅሣሥ ወር ላይ ሲሆን፤ ከመታገዱ በፊት ሚያዝያ 5 ላይ ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ ነበር። አሁን ላይ ጉዳዩ ኒው



ኦርሊያንስ ወደሚገኘው የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይመለሳል።

የቃል ክርክሩም ለረቡዕ ቀጠሮ ተይዞለታል። በክርክሩ ማንም ቢያሸንፍም ጉዳዩን ወደ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መልሶ የመውሰድ አማራጭ አለ።

ሪፐብሊካኖች ብዙውን ጊዜ የዲሞክራቱን ባይደን አስተዳደር የአሜሪካ-ሜክሲኮን ድንበር በሚይዙበት አግባብ ይወቅሷቸዋል። ኅዳር ላይ ከሚካሄደው የዋይት ሐውስ ምርጫ በፊት ይህ የሕዝብ አስተያየት መኖሩም ለመራጮች ትልቅ ስጋት ነው።

የካቲት ወር ላይ በአሜሪካ ተቋም በተሰበሰበ የሕዝብ አስተያየት መሠረት አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት አሜሪካውያን ስደት፣ ኢኮኖሚ እና የዋጋ ንረት የአገሪቷ ትላልቅ ችግሮች እንደሆኑ ያምናሉ።

ባለፈው የታኅሣሥ ወር በሺዎች የሚቆጠሩ ከማዕከላዊ እና ደቡብ አሜሪካ አገራት የተውጣጡ ስደተኞች በእግራቸው ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ድንበር ማቅናታቸው የሚታወስ ነው።

ሕፃናትና አዋቂዎች ሳይቀሩ የተሰባሰቡበትና ስምንት ሺህ ገደማ የሚሆኑ በአብዛኛው ከቬንዝዌላ፣ ኩባ እና ሜክሲኮ የመጡ ስደተኞች ናቸው ወደ አሜሪካ ድንበር አቅንተው በርካታ ውዝግብ መፈጠሩ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# የሸማቾች ቀን ስናስብ...

**ማጠቃለያ**

ቢቸግረኝና ስለሸማቾች ላለፉት አራትና አምስት ዓመታት ወትውቼ ወትውቼ አባ ከና የሚለኝ ባጣ፤ እየተከበረ የሚገኘውን የሸማቾች ሳምንት ምክንያት በማድረግ የዛሬውን መጣጥፌን በማጠቃለያ ጀምሬያለሁ።

የግብይት ሰንሰለቱን በማሳጠር አምራችና ሸማችን በቀጥታ በማገበያየት፤ በየደረጃው የተሰገሰገውን ደላላ ከግብይት ሥርዓቱ በማስወጣት፤ የንግድና የመኖሪያ ቤት ኪራይን በመተመንና ጣሪያ በማስቀመጥ፣ የትርፍ ሕዳግን በመወሰን፤ ገበያውን ለውጭ ኩባንያዎች በመክፈት፤ በሀገሪቱ ሰላምንና መረጋጋትን በማረጋገጥ፤ በአጠቃላይ በግብይት ሥርዓቱ የሕግ የበላይነትን በማስፈን አሁን ያለውን የዋጋ ግሽበትና እሱን ተከትሎ የመጣውን የኑሮ ውድነት ቢያንስ ከግማሽ በላይ መቀነስ ይቻላል።

የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት በዚያ ሰሞን ይፋ ያደረገው የጥናት ግኝት ይሄን ያረጋግጣል። ምርት ሸማቹ ጋር የሚደርሰው 58 በመቶ ተጨምሮበት ነው። የሚያሳዝነው የግብይት ሰንሰለቱ አምራቹንም ሆነ ሸማቹን ተጠቃሚ የማያደርግና ሁልጊዜ ብልጭ እንዲወሰድባቸው ክፍተት ያለው ነው። ይህ የ58 በመቶ ጭማሪ እሴት በማይጨምሩ ስግብግብ ደላላዎች ኪስ የሚገባ ነው።

መንግሥት በግብይት ሥርዓቱ የሕግ የበላይነትን በማስፈን ብቻ የዋጋ ግሽበቱንና እሱን ተከትሎ የሚመጣውን የኑሮ ውድነቱን ከግማሽ በላይ መቀነስ ይችላል። ምንም እንኳ ሌሎች ከዚህ በላይ ነው ቢሉ ይፋዊ አኀዞች የሀገራችንን የዋጋ ግሽበት እስከ 30 በመቶ ያደርሱታል። ይህንን ተከትሎም መንግሥት ደላላውን ከግብይት ሰንሰለቱ በማስወጣት፤ ሕገ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን በማስቆምና የኪራይ ቤት ተመንና ጣሪያን በመወሰን ቢያንስ የዋጋ ግሽበቱን ቀንስልን የሚሉ ድምጾች ብዙ ናቸው።

ሸማቹ ስለ መብቱ ግንዛቤ ኖሮት መብቱን እንዲያስከብርና በተዘዋዋሪ ደግሞ ጫናውን እንዲቀንስልህ የንግድ ውድድርና የሸማቾች መብት ጥበቃ ባለሥልጣን ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አውጥቶ ራሱን በቻለ ባለሥልጣን ተቋም እንደመራ የሚጠይቁም አሉ። አደረጃጀቱ በራሱ የጥቅም ግጭት ሊፈጥር ስለሚችል ነው። በሚኒስቴሩ ስር ሆኖ የንግድ ውድድርን እንዴት ሊያሳልጥና ስለሸማቹ መብት ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ሊቆም ይችላል ከሚል እሳቤ በመነሳት ነው። ይህም የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣንና ኢትዮ ቴሌኮምን በአንድ መሥሪያ ቤት እንደማደራጀት ነው የሚሉም አሉ። ይህንን ለጊዜው እንተወውና ወደ ተነሳሁበት ሃሳብ ልመለስ።

የዓለም የሸማቾች ቀን ባለፈው ዓርብ መጋቢት 6 ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ41ኛ በኢትዮጵያ ለ11ኛ ጊዜ ተከብሯል። "ፍትሐዊና ኃላፊነት የሚሰማው የሰው ሠራሽ አስተውሎት ወይም /AI/ ለሸማቾች" በሚል መሪ ቃል ተከብሮ ውሏል በሀገራችን ደግሞ የሸማቹን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ለማስገባት በሞከረና በደምሳሳው፤ "በኅብር መብታችንን እናስከብር" በሚል ድፍን ያለና ግልጽ ያልሆነ መሪ ቃል ታስቦ ውሏል።

የንግድና ቀጣናዊ ሚኒስቴር "በኅብር መብታችንን እናስከብር" ሲል የትኛውን መብት እንደምናስከብር አልገለጸልንም። "ሸማች" የሚለውን ቃል ተጠቅሞ "በአንድነት የሸማቾችን መብት እናስከብር" ቢለን ትርጉም ይሰጠን ነበር። እንዳለመታደል ሆኖ የሸማቾች ቀን መሪ ቃል "ሸማቾች"ን ገድፎ ውሏል። እንዲህ ሸፋፍኖና አድበስብሶ ማለፍ ለምን እንዳስፈለገ ሚስጥሩን የሚያውቀው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ነው።

እኤአ መጋቢት 15 ቀን 1962 ዓ.ም 35ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ ለአሜሪካ ኮንግረስ ስለ ሸማቾች መብት ተናገሩ። በዚህ ንግግራቸው "ሁሉም ሸማች ነው" ማለታቸውም ሲታወስላቸው ይኖራል። ይቺ ታሪካዊት ቀን የአንድ ሀገር መሪ በተለይ ስለሸማቾች ለመጀመሪያ ቀን የተናገረባት ዕለት ስትሆን ከ21 ዓመታት በኋላ የመንግሥታቱ ድርጅት እኤአ መጋቢት 1983 ዓ.ም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ላከበረው የሸማቾች ቀን እርሾ ሆና አገልግላለች።

በዓለም የሸማቾች መብት ቀን ሸማቹ እንዳይጭበረበር፣ እንዳይታለል፣ አድልዎና ብዝበዛ እንዳይፈጸምበት ስለመብቱ በተለይ የሚመከበርበት ዕለት ነው። ይሁንና ሸማቹን የማብቃትና የማስገንዘብ ሥራዎች ዓመት ሳይጠበቅ በየእለቱ ሊከናወኑ ይገባል። የሸማቾችን መብት ማስከበር አጉራ ዘለል የሆነውን የግብይት ሥርዓት አደብ ለማስገዛት አቅም ስለሚፈጥር በቅንጅት በተከታታይነት ሊሰራበት ይገባል።

ሸማቾች በግብይት ሥርዓቱ የሚደርስባቸውን የመብት ጥሰት ለመከላከል በትብብር መሥራት እንደሚገባ፤ በሚኒስቴሩ የሀገር ውስጥ ንግድ ሸማቶች ጥበቃ መሪ ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሮ መስከረም ባሕሩ፤ ሸማቾች በግብይት ሥርዓት ላይ እየደረሰባቸው ያለውን የመብት ጥሰት ለመከላከልና በቅንጅት መሥራት ይገባል ሲሉ ጥሪ አድርገዋል። ሸማቹ ገዝቶ በሚጠቀመው ምርት የጤና ችግር እንዳያስከትልበት የመጠበቅ ሥራ እየተሠራ መሆኑን አመላክተው፤ በንግድ ሥርዓት ውስጥ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ሸማች በመሆኑ በሚገዛው ምርት ጤንነቱ የተጠበቀ፤ ስለምርቱ በቂ መረጃ ያለው፤ የመምረጥ መብቱ የተከበረ፣ የመደመጥና ያለመግዛት መብቱ በሰፊው እንዲከበር መሥራት ይገባል።

ሸማቾች በሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ትልቅ ሚና ያላቸው በመሆኑ በግብይት ሂደት ላይ በሕግ የተቀመጠላቸው መብት ሊከበርላቸው ይገባል ሲሉ አሳስበዋል። ሸማቶች አንድ ምርት ገዝተው በመጠቀም የደረሰባቸው ጉዳት ካለ የመካስ መብት አላቸው ያሉት ወይዘሮ መስከረም፤ ሸማቹ ማኅበረሰብ መብቶቹን አውቆ ለሚደርስበት የመብት ጥሰት ጥብቅና መቆም እንዳለበት ጠቁመዋል።

በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሸማቾች መብት ጥበቃና ግንዛቤ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሰይፉ አየለ በበኩላቸው፤ ነጋዴው ማኅበረሰቡን እንዲያገለግል፣ ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ እንዲያደርግ፣ ገበያውን የሚመጥን ምርት እንዲያቀርብ የሚያስገድድ ሕግ መኖሩን ገልጸዋል። የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፉባቸው ምርቶች ለገበያ ቀርበው በሸማቹ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ፤ በሀገር ውስጥ የሚመረቱና ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ እየተሠራ ነው፤ በሸማቾች ላይ እየደረሰ ያለውን የመብት ጥሰት ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

በሌላ በኩል በሀገሪቱ እየተስፋፋ ያለውን የንግድ እንቅስቃሴ ተከትሎ በገበያ ላይ የሸማቾችን ጤንነትና ደህንነት የሚጎዱ ተግባራት እንዳይፈጠሩ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የፀረ ውድድርና የሕግ ጥሰት መከላከል ዴስክ ኃላፊ አቶ ጌትነት አሸናፊ ተናግረዋል። ከባዕድ ነገሮች ጋር የተቀላቀሉ፤ የአገልግሎት ዘመን ያለፈባቸው፤ ደረጃቸውን ያልጠበቁና የአገልግሎት ጊዜያቸው አልፎ እንደ አዲስ ለገበያ እንዲውሉ የሚደረጉ ምርቶች አሉ ሲሉ ያስጠነቀቁት ኃላፊው፤ ምርቶች ገበያ ላይ ውለው የማኅበረሰቡ ጤና ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ የመከታተልና የመቆጣጠር ሥራ እየተሠራ መሆኑንም ገልጸዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮና የሸማቾች መብት ጥሰት ጥበቃ ማኅበር፣ ከፌዴራል ወንጀል ምርመራ ቢሮ ጋር የሸማቾች መብት በተመለከተ ውይይት በማድረግ የሸማቾችን ቀንን ማክበሩን የ"አዲስ ዘመን"ጋዜጣ ዘጋቢ ታደሠ ብናልፈው አስነብቦናል። የሸማቾች ሳምንት ነውና በነካ እጄ አንዳንድ ነጥቦችን ላነሳሳ ወደድሁ።

**ሸማቾች በሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ትልቅ ሚና ያላቸው በመሆኑ በግብይት ሂደት ላይ በሕግ የተቀመጠላቸው መብት ሊከበርላቸው ይገባል ሲሉ አሳስበዋል**

ዋጋ ለመጨመር የእጥፍ እጥፍ አንዳንዴም ከዚያ በላይ በማትረፍ ሸማችን ለመግፈፍ ሰበብ አስባብ የሚፈልጉ ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት እና ደላሎች አሉ። ጨዋና ለወገናቸው የሚራሩ ጥቂት ነጋዴዎች መኖራቸው እንዳለ ሆኖ። እንደ ሀገር የገጠመንን የውጭ ምንዛሬ እጥረት እና መጀመሪያ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል አሁን ደግሞ በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች የሚካሄዱ ጦርነቶችን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም በአቋራጭ በአንድ ጀምበር ለመክበር ሥራዬ ብለው የሚታትሩ ሥነ ምግባር የጎደላቸው ነጋዴዎች አሉ።

እነዚህ ስግብግብ ነጋዴዎች ኮቪድ የገባ ጊዜ የማስክና የሳንታይዘርን ዋጋ የት አድርሰውት እንደነበር አንዘነጋም። በተለይ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ በፍጆታ ሸቀጦችና እንደ ትምህርትና ጤና አገልግሎቶች ላይ የምናስተውለው ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ የአንድ ሀገር ዜጎች መሆናችንን እስከ መጠየቅ የሚያደርስ ነው።

ሰሞኑን ጤፍ በኪሎ 156፣ ካሮት 80 ብር፣ ድንች 40 ብር፤ ዘይት ባለ አምስት ሊትሩ 1050 ብር የገባ ሲሆን በአንጻሩ ባልተለመደ ሁኔታ በአብይ ጾም ወቅት ይጨምሩ የነበሩ ሽንኩርትና ቲማቲም ቅናሽ አሳይተዋል። አሁን ሸማቹን እየፈተነና እያማረረ ያለው በዚህ አራት ዓመት በኪሎ 50 ብር የነበረ ጤፍ ከሶስት እጥፍ በላይ ወይም ከ300 በመቶ በላይ ጨምሮ እስከ 156 ብር መግባቱ ነው። በአናቱ ከአምስት ዓመት በፊት ሁለትና ሶስት ሺህ የነበረው ባለ አንድ መኝታ የጋራ መኖሪያ እስከ 16,000 ብር መሰቀሉ እየተነገረ ነው።4500 ብር የነበረ የሱቅ ኪራይ አሁን 45,000 ገብቷል።

ይህ ዋጋ የካ አባዶና አያት አካባቢ ሲሆን መሐል ከተማ ደግሞ ከዚህ እጅግ ይንራል። በነገራችን ላይ የግለሰብ የኪራይ ቤቶችም በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶም ሆነ ተሰምቶ በማያውቅ ፍጥነት ጣራ ነክተዋል። በሥራና ከተማ ልማት ተረቆ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚገኘው የቤት ኪራይ አዋጅ ፈጥኖ ወደ ሥራ እንዲገባ እየተወተወተ ያለው ለዚህ ነው። የአዲስ አበባ አስተዳደር የቤት ኪራይ ደንብ አርቅቋል ቢባልም ጸድቆ ወደ ሥራ ባለመግባቱ በየሶስት ወሩ የቤት ኪራይ ጭማሬን የሚያግድ ውሳኔ ማሳለፍ ላይ ተጠምዷል። የቤት ኪራይ ውድነት እንደ ነዳጅ አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት እና እሱን ተከትሎ የሚመጣውን የኑሮ ውድነትን እያባበሰ ስለሆነ መፍትሔ ሊፈለግለት ይገባል።

የአሜሪካው 35ኛ ፕሬዚዳንት ጆን ኦፍ ኬኔዲ በአንድ አጋጣሚ "ሁሉም ሸማች ነው። በግሉም ሆነ በመንግሥት ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎች በአውንታዊም ሆነ በአሉታዊ አግባብ ጥቅሙ የሚነካ፤ በሌላ በኩል የሸማቹ ውሳኔ በግሉም ሆነ በመንግሥት ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎች ላይ ተፅዕኖ መፍጠር የሚችል ነው።" ሲሉ ሸማች በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካውና በማህበራዊ እርካቦች የተቆናጠጠውን ከፍታ አመላክተዋል። ከዚህ የፕሬዚዳንቱ ትርጓሜ ሁለት አበይት ሰበዞችን መምዘዝ ይቻላል። የመጀመሪያው አንተም፣ አንችም፣ እኔም ሁላችንም ሸማች መሆናችንን። በሆነ አጋጣሚ ሻጩ ሸማች፣ ሸማቹ መልሶ ሻጭ ይሆናል። ሁለተኛውና ትልቁ መልዕክት በሸማቹ፣ በሻጩ እና በመንግሥት መካከል ያለውን ሚዛናዊ እና ፍትሐዊ ግንኙነት የሚያወሳ ነው።

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1986 ይፋ የሆነው የሸማቾች ጥበቃ ሕግ "ማንኛውንም ሸቀጥ ወይም አገልግሎት የሚገዛ ሸማች ነው።" በማለት ይተረጉማል። ይህ ፕሬዚዳንት ኬኔዲ "ሁላችንም ሸማች ነን።" ካሉት ጋር ይቀራረባል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በ1993 ዓ.ም ያሳተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ደግሞ ሸማችን ጠበብ አድርጎና አኮሳምኖ "እህልን ለንግድ ሳይሆን ለምግብነት የሚገዛ በላተኛ።" ሲል ይበይነዋል። የአገልግሎት ሸመታውን በዘነጋ መልኩ። የእንግሊዘኛው ሜሪያም ዌብስተር መዝገበ ቃላት ደግሞ ቅንብብ አድርጎ "ሸቀጦችንና አገልግሎቶችን የሚገዛ ሰው ሸማች ነው።" (consumer a person who buys goods and services) በማለት ይተረጉመዋል። ሸማችነት ሸቀጥንም አገልግሎትንም እንደሚያካትት ባረጋገጠ ሙሉዑ ብያኔ ይሰጠዋል።

ወደ ሀገራችን ስንመጣ በሸማቹ፣ በሸቀጥና አገልግሎት ሻጭ መካከል ያለው ግንኙነት የተዛባ፣ ኢፍትሐዊ፣ መርህ አልባ እና ኢ-ዴሞክራሲያዊ ነው። መንግሥትም ሆነ ሻጭ የየራሳቸውን ፍላጎትና ጥቅም ለማስከበር ይተጋሉ እንጂ ለሸማቹ ያን ያህል ደንታ የላቸውም ማለት ይቻላል። በተለይ መንግሥት በ"የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው" አባዜ ሻጭ ላይ የሚፈጥራቸው ማናቸውም ጫናቸው መዳረሻቸው ሸማቹ እንደሆነ ሆዱ እያወቀ እንኳ ጫናውን ቀለል ለማድረግ አጥጋቢ ጥረት ሲያደርግ አይስተዋልም።

ከአስርና ከዚያ በላይ ተከታታይ ዓመታት የተመዘገበው "ዕድገት" መንግሥት ከፍተኛ ካፒታል በማፍሰስ ዕውን ያደረገው ስለነበር እና የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ስለነበር ለተከታታይ አስር እና ከዚያ በላይ ዓመታት የዋጋ ግሽበቱ በሁለት አኀዝ ቀጥሏል። የታክስ ፖሊሲውም ሸማቹን ለተደጋጋሚ ታክስ የሚዳርግ ከመሆኑ ባሻገር ሻጩ ላይ የሚጣል የታክስ ግብር የማታ ማታ እንደ ትኩስ አሎሎ ወደ ሸማቹ የሚወረወር ከሆነ ውሎ ሰንብቷል። የግብር መሠረቱን ከማስፋት ይልቅ በተወሰኑ የግብር ዘርፎች ላይ የሙጥኝ መባሉም ለችግሩ ተጨማሪ አቅም በመሆን "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" ሆኗል።

ሻሎም ! አሜን×፫።

# ስፖርት





## ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ የደመቀችበት የአፍሪካ ጨዋታዎች

**ዓስማየሁ ግዛው**

በፓን አፍሪካን ተምሳሌትነትና በኦሊምፒክ መርህ መሠረት የሚካሄደው የአፍሪካ ጨዋታዎች ለ13ኛ ጊዜ በጋና አስተናጋጅነት መካሄደ ከጀመረ ሰንብተል። ውድድሩ ወደ መገባደጃ በተቃረበበት በዚህ ወቅትም ኢትዮጵያ በተለያዩ የአትሌቲክስ ውድድሮች በወርቅ ሜዳሊያዎች መድመቅ ቀጥላለች።

በበርካታ የስፖርት አይነቶች ተሳታፊ ሀገራት እየተፋለሙ፣ አሸናፊዎችም የሀገራቸውን ሰንደቅ ከፍ አድርገው እያውለበለቡ ይገኛሉ። ተሳታፊ ሀገራት እንደየአቅማቸው በተካኑባቸው ስፖርቶች ሜዳልያዎችን እየሰበሰቡ ብቃታቸውንም እያስመለከቱ ይገኛሉ። ኢትዮጵያም ከሌሎች ሀገራት አኳያ የምትሳተፈው በጣት በሚቆጠሩ ስፖርቶች ቢሆንም፤ በአትሌቲክስ ግን ግሩም የሚባል ድል እያስመዘገበች በሜዳሊያ ሰንጠረዡ ደረጃዋን ለማሻሻል ጥረት እያደረገች ነው።

በቦክስ፣ ብስክሌት፣ ጠረጴዛ ቴኒስ እና ውሃ ዋና ስፖርቶች አንጻራዊ ፍክክርን ማድረግ የቻለው ኢትዮጵያ በአትሌቲክሱ አስደማሚ ድሎች ማስመዝገቧን ቀጥላለች።

በሴቶች 5ሺ ሜትር የተጀመረው የአረንጓዴ ጎርፍ ድል በወንዶች 3ሺ ሜትር ወርቁን ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት መከተሉ ይታወሳል። ኢትዮጵያ በተካፈለችባቸው የአጭር ርቀትና የሜዳ ተግባራት ውድድሮች ስኬታማ ባትሆንም በተለመዱት የመካከለኛና ረጅም ርቀት ሩጫዎች ግን ሌሎች ድሎች ተከታትለው በመገኘታቸው በደረጃ ሰንጠረዡ ለውጥ አምጥታለች።




**በ10ሺ ሜትር የወርቅና ብር ሜዳሊያ ያገኙት አትሌት ንብረት መላክ እና ገመቹ ዲዳ፤**

ሦስተኛው የወርቅ ሜዳሊያ ኢትዮጵያ እምብዛም በማትታወቅበት የ800 ሜትር የሴቶች ውድድር በወጣቷ አትሌት ጽጌ ድጉማ ማክሰኞ ምሽት ተመዝግቧል። በቅርቡ ግላስጎው ላይ በተካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና ላይ በርቀቱ ታሪክ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ የወርቅ ሜዳሊያ ያጠለቀችው ጥቁሯ ፈርጥ አትሌት ፅጌ ዱጉማ፤ በርቀቱ ያላት ተስፋ በግልጽ የታየ ነበር። ጠንካራዋ አትሌት በምትታወቅበት ድንቅ ብቃትና አጨራረስ በሳምንታት ልዩነት ሁለተኛውን የርቀቱን ድል በአፍሪካ ጨዋታዎች ለማስመዝገብ ችላለች። ከቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የተገኘችው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አትሌት ጽጌ ርቀቱን በ1:57.73 ሰዓት ማጠናቀቅ የቻለች ሲሆን፤ ግላስጎው ላይ ከገባችበት 2:01.90 የሆነ ሰዓት ብልጫ ያለውም ነው። በርቀቱ አብረዋት የተሳተፉት አትሌት አዳኑ ኔንቆ እና አስቴር አሬሬ ደግሞ ስምንተኛ እና ዘጠነኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቀዋል።

ቀጣዩ ድል በ10ሺ ሜትር የወንዶች ውድድር የተመዘገበ ሲሆን፤ የወርቅና የብር ሜዳሊያዎቹ ወደ ኢትዮጵያ ገቢ ሆነዋል። አመሻሽ ላይ በተካሄደው የፍጻሜ ውድድር በእልህ አስጨራሽ ፍልሚያ አስቀድመው ትኩረት ያገኙት ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች አሸናፊ ሆነዋል። በርካታ ጠንካራና ልምድ ያላቸው አትሌቶች በተፎካከሩበት መድረክ አትሌት ንብረት መላክ አሸናፊ በመሆን የወርቅ ሜዳሊያውን አጥልቋል። አትሌቱ ውድድሩን ለማጠናቀቅ የፈጀበት ሰዓት 29፡45፡37 ሲሆን፤ ተከትሎት ከገባው የሀገሩ ልጅ ጋር አትሌት ገመቹ ዲዳ ጋር ያለው የሰዓት ልዩነት የማይክሮ ሰከንዶች ብቻ መሆኑ ፉክክሩ ከፍተኛ እንደነበር ማሳያ ነው። አትሌት ገመቹ ዲዳ የሁለተኝነቱን ደረጃ በመያዝ የብር ሜዳለያውን ሲያገኝ የገባበት ሰዓት ደግሞ 239፡45፡68 በመሆን ተመዝግቧል። ጠንካራ ተፎካካሪያቸው የነበረው ኬንያዊ አትሌት ኢቫንስ ኪፕቱም ደግሞ 29፡47፡61 በሆነ ሰዓት በመግባት የነሐስ ሜዳሊያውን ወስዷል።

ኢትዮጵያ ካሰለፈቻቸው ጠንካራ አትሌቶች አንዱ የሆነው ኃይለማርያም አማረ ደግሞ ውድድሩን 7ኛ በመሆን ፈጽሟል።

ትናንት ሜዳሊያ የተመዘገበበት የአትሌቲክስ ውድድር ርምጃ ሲሆን፤ በወንዶች የወርቅ በሴቶች ደግሞ የብር ሜዳሊያው ተገኝቷል። ትናንት ረፋድ ላይ በተካሄደው የ20 ኪሎ ሜትር ርምጃ ውድድር ኢትዮጵያ በሁለቱም ጾታዎች ሦስት ሦስት አትሌቶችን አሰልፋለች። በዚህም በወንዶች ምስጋና ዋቁማ አምስተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ ለሀገሩ አስመዝግቧል። የብር ሜዳሊያው ደግሞ በሴቶች ተመሳሳይ ውድድር በአትሌት ስንታየሁ ማስሬ የተመዘገበ ሆኗል።

የአፍሪካ ትልቁ የውድድር መድረክ የሆነው የአፍሪካ ጨዋታዎች 39 ሀገራት የሜሊያ ሰንጠረዡ ውስጥ መግባት ችለዋል። ኢትዮጵያም እስከ ትናንት ረፋድ 10 ሜዳልያዎችን ማስመዝገብ ችላለች። ከእነዚህ ሜዳሊያዎች አብዛኞች የተመዘገቡት በአትሌቲክሱ ሲሆን፤ 5 የወርቅ፣ 3 የብር እና 1 የነሐስ ሜዳሊያዎች ተገኝተዋል። በብስክሌት ስፖርት ደግሞ 1 የብር ሜዳሊያ በማስመዝገብ ከአትሌቲክስ ቀጥሎ ስሙ ሰፍሮ ይገኛል።


### የጨረታ ማስታወቂያ

የሀዲያ ዞን ፋይናንስ መምሪያ ለ2016 በጀት ዓመት የተለያዩ ሞዴል ላላቸው ተሽከርካሪዎች (መኪናዎች) ጎማዎችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

**ስለሆነም፡-**

1. በመስኩ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸው፣
2. የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ያላቸው፣
3. የቫት ተመዝጋቢነት ሰርተፍኬት ያላቸው፣
4. የዕቃና አገልግሎት አቅራቢነት ሰርተፊኬት ያለው፡፡

ሀዲያ ዞን ፋይናንስ መምሪያ ቢሮ ቁጥር 17 በአካል በመምጣት የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ብር 100.00/አንድ መቶ ብር/ በመክፈል እንድትገዙና ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ብር 60,000.00/ስልሳ ሺህ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ/CPO/ በማሰራት ማስያዝ የሚጠበቅባቸው ሲሆን የጨረታ መወዳደሪያ ዋጋ መምሪያው ባዘጋጀው ፎርማት ላይ ብቻ በመሙላት ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት የመወዳደሪያ ፖስታዎችን ኦርጂናልና ኮፒ ለየብቻ በማሸግ ቢሮ ቁጥር 17 በሚገኘው የጨረታ ሳጥን ውስጥ እንድታስገቡና ጨረታውም በ16ኛው ቀን ከጧቱ 4፡00 ሰዓት ላይ የጨረታ ሳጥን ታሽጎ በ4፡30 ሰዓት ላይ የሚከፈት ሲሆን ቀኑ የበዓል ወይም የዕረፍት ቀን ከሆነ በቀጣይ ቀን በተመሳሳይ ሰዓትና ቦታ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ መስሪያ ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ፡- በስልክ ቁጥር 0461784281 ደውሎ መጠየቅ የሚቻል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት የሀዲያ ዞን ፋይናንስ መምሪያ**

### የጨረታ ማስታወቂያ

የአርብቶ አደር አካባቢ የመስኖ ተቋማት ጥገና፣ አስተዳደር እና አጠቃቀም ቱርሚ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በኛንጋቶም ወረዳ ናፕትኮይት መስኖ ተቋም በግንብ ለሚያስገነባው የመስኖ ካናል (Lined canal) አገልግሎት የሚውል የድንጋይና አሸዋ አቅርቦት በግልጽ ጨረታ ከዚህ በታች ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 5 በተዘረዘሩት ልክ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት ተጫራቾች

1. በመስኩ ህጋዊ ፍቃድ ያለውና የዘመኑን ግብር የከፈሉ፤
2. የጨረታ ማስታወቂያው ለ 15 ተከታታይ ቀናት አየር ላይ ይውላል፣
3. ጨረታው የሚከፈተው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ16ኛው ቀን ከጥዋቱ 4፡00 ታሽጎ 4፡30 ይከፈታል፤
4. የሰነዱ ሽያጭ በነጻ ሲሆን ፣
5. ጨረታው የሚከፈተው ደቡብ ኦሞ ዞን ቱርሚ ከተማ አስተዳደር ፕሮጀክት ጽ/ቤት ነው !

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር** +251-927150138 ይደውሉ

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት መስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ቢሮ የአርብቶ አደር አካባቢ የመስኖ ተቋማት ጥገና አስተዳደርና አጠቃቀም ፕሮጀክት ጽ/ቤት**